# ኢትዮጵያዊ ፊደል ለሀገር በቀል ቋንቋዎቻችን ያለው ፋይዳ

ሙሉጌታ ሥዩም*

Abstract

Ethiopia is a home land of communities speaking diversified languages and an ancient country which has been using its own script and writing system. Ge'ez is the first written language with its own script in the country. Later Amharic developed its own writing system adopting it from Ge'ez language. Currently, The Ge'ez script, known as the Ethiopic script or fidel, is used for several Ethiopian languages that have developed their writing system based on it such as Tigrigna, Harari, Argoba, Gurage, etc. The main objective of this study is to investigate and analyze the potential of using fidel for any of the indigenous languages spoken in the country. The study presents linguistic criteria used in the selection of a script for any language and presents that the Ethiopic script or fidäl is a viable candidate for use for Ethiopian languages. The data for the study were gathered from both primary and secondary sources and employed the computational theory of writing systems as a theoretical framework. The study presents a brief overview of African writing systems and the patterns and rationale behind script choice in writing Ethiopian languages in the past two decades and half. The study outlines the linguistic as well as nonlinguistic criteria that are considered in the development of orthographies. Based on these criteria, the study presents how the Ethiopic script is a viable option for writing Ethiopian languages. The study argues against the narratives that led to the choice of Latin script as a basis of orthography development in Ethiopia.

Key words: Ethiopic script, Latin script, Writing systems.

*ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ ሥዩም በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ባህሎች አካዳሚ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው።

# ፩. መግቢያ

## ፩.፩. የጥናቱ መነሻ ንድፈ ሐሳብ

ከሕፃንነቴ ጀምሮ ፊደል ቆጥሬ ንባብ ተምሬ በቄስ ትምህርት ቤት ያለፍኩ በመኾኑ ለፊደል ልዩ ፍቅር አለኝ፡፡ ኾኖም የበለጠ ለኢትዮጵያ ፊደል ልዩ ትኩረት እንድሰጥ ያደረገኝ ጉዳይ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርቴን ኒዘርላንድ ከሠራሁ በኋላ የገጠመኝ ክሥተት ነው፡፡ በኔዘርላንድ ሌይደን ዩኒቨርስቲ የሦስተኛ ዲግሪ የሥነ ልሳን ትምህርቴን የተከታተልኩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው፡፡ የመመረቂያ ጽሑፍ ጥናቴ ደግሞ በዲሜ ቋንቋ ሰዋሰው ላይ ነው፡፡ ይህ ቋንቋ በሀገራችን ደቡብ ክፍል የሚነገረው የኦሞቲክ ቋንቋ ቤተሰብ ነው፡፡ የቋንቋውን ሰዋሰው ያጠናሁትና የጻፍኩትም የእንግሊዝኛ ቋንቋን በመጠቀም ነው፡፡ እኔን ካማከሩኝ ፕሮፌሰሮች አንዷ ሴት ኢትዮጵያዊት አማርኛ እና ወላይትኛ ተናጋሪ ስትኾን ሁለተኛው አማካሪዬ ደግሞ ኔዘርላንዳዊ ደች ቋንቋ ተናጋሪ ነው፡፡ ሁለቱም በጣም መልካም ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሁለቱም እኔን ያማከሩበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ኾኖ ሳለ ትምህርቴን አጠናቅቄ በጥሩ ኹኔታ ስመረቅ ግን ሌይደን ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ትምህርት መረጃ ሰርተፊኬቴን አዘጋጅተው የሰጡኝ በደች ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሳይኾን በጥንታዊው የላቲን ቋንቋና ፊደል የተጻፈ ነበር፡፡ እኔን እንድማር በመርዳታቸው ባመስግናቸውም ፈጽሞ ልረዳውም ላነበውም በማልችለው ቋንቋና ፊደል የትምህርት መረጃዬን መስጠታቸው ለእኔ እንግዳ ነገር ነበር የኾነብኝ፡፡ በጣም እየገረመኝ ወደ ሀገሬ ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ የትምህርት መረጃዬን ይዤ ወደ ዩኒቨርስቲ ሳቀና የትምህርት መረጃህ በጥንታዊው የላቲን ፊደል የተጻፈ በመኾኑ የሚረዳው ስለሌለ መተርጎም አለበት ተባልኩ፡፡ የትምህርት መረጃዬን አስተርጉሜ ለማቅረብ በከተማው ውስጥ ወደሚገኙ የትርጉም ቢሮዎች ተጓዝኩ ኾኖም አንድም ጥንታዊውን የላቲን ፊደል አንብቦ ሐሳቡን ተረድቶ ወደ እንግሊዝኛ ወይም ወደ አማርኛ ሊተርጉምልኝ የሚችል ባለሙያ ሰው ላገኝ አልቻልኩም፡፡ ብዙ ቀናት ተንከራተትኩ ሊሳካልኝ አልቻለም፡፡ ቢቻል በተማርኩበት ቋንቋ በእንግሊዝኛ ካልኾነ ደግሞ የሀገራቸው የሥራ ቋንቋ በኾነው ደች የሚሉት የኔዘርላንድኛ ቋንቋ አዘጋጅተው የትምህርት መረጃዬን መስጠት ሲገባቸው እኔ በማላውቀውና ባልተማርኩበት ሰውም በቀላሉ ሊያነበውና ሊገባው በማይችልበት በጥንታዊው የላቲን ቋንቋና ፊደል ጽፈው የሰጡኝ ምን ይኹን ብለው ነው ብዬ እያሰብኩ ብዙ ቀናትያለመፍትሔ ሰነበትኩ። በዚሁ ሐሳብና ጭንቀት ውስጥ ሳለሁ የጥንታዊው ላቲን ቋንቋና ፊደል ሊቅ የኾነው ጣሊያናዊው ሰው ፕሮፌሰር ማራሲኒ ድንገት ተማሪዎች ለመፈተን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መጥቶ ተገናኘን፡፡ እኔም ቀደም ሲል እርሱንም ሙያውንም ዐውቅ ስለ ነበረ ጉዳዩን ገልጬ ነገርኩት፡፡ እርሱም እኔን ያስጨነቀኝ ይህ የትርጉም ሥራ ለርሱ

ቀላል እንደ ኾነ ነግሮ አረጋጋኝ፡፡ ወዲያው ኮፒ አድርጌ ዶክምንቱን ሰጥቼው ከትርጉም ቢሮዎቹ ጋር ተነጋግረን ርሱን ተጠቅመው በአንድ ቀን ውስጥ የትርጉሙ ሥራ በርሱ ተከናወነና ችግሩ ተቃለለ፡፡ ለጊዜው የዩኒቨርሲቲው (የላይደን ዩኒቨርሲቲ) አሠራር ግር ቢለኝም ቀስ እያልኩ ሳስበው ግን የራሳችን ነው ብለው ለሚያምኑበት ለጥንታዊው ለላቲን ፊደልና ቋንቋ የሰጡት ትልቅ ቦታ መኖሩን፣ ያንንም በተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመው በዓለም ከሚያስተዋወቁባቸው ስልቶቻቸው አንዱ መንገድ የእኔን እና የመሰል ጓደኞቼን የመመረቂያ ሰነድ በጥንታዊው የላቲን ፊደል ጽፎ መስጠት መኾኑ ገባኝ፡፡ አሁን የበለጠ ሲገባኝ የማንነታቸው መገለጫ ለኾነው ቅርሳቸው፣ለፊደላቸውና ለቋንቋቸው የሰጡት ክብር አስቀናኝ፡፡ እነርሱ መላው አውሮፓን በላቲን ፊደል እየተጠቀሙ አልበቃ ብሏቸው መላው አፍሪካን በቅኝ ግዢ ተጽእኖ ሀገር በቀል ፊደላቸውን አጥፍተው ወደ ላቲን ጠቅልለዋቸዋል፡፡ ቢሳካላቸው የቻይናን እና የጃፓንን ፊደላትም አጥፍተው ሊጠቀልሉ ይፈልጋሉ ይጥራሉ፡፡ እኛም ከአፍሪካ የቅኝ ግዢ ዳፋ ነጻ ነን ብለን ብንፎክርም ሐቁ ግን የሚያሳየው የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ቋንቋና ፊደላችንን አጥፍተው ወደ ራሳቸው ወደ ላቲን ለመውሰድ የፊደል ወረራ እያደረጉ የሥነ ልቡና ጦርነት ከፍተውብናል፡፡ ይህን ለመተግበር ያላቸው ስልትና ትጋታቸው ደነቀኝ፡፡ በሀገራችን በርዳታ ስም በልማት ሥራ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ስብከትና ትርጉም ስም የሚኀርፉት መንግሥታዊ ያልኾኑ ድርጅቶች ትጋታቸው ፊደልን ለመደምሰስ ላቲንን ለማንገሥ መኾኑን ስለ ተረዳሁ የምርምር ሥራዬን በፊደል ላይ ቀጠልኩ፡፡ እኔም በፍጹም ኢትዮጵያዊነት ወኔ በሞያዬ በምችለው ሁሉ ስለ ፊደል ለመናገር ለመጻፍ ለማጥናት ለማስተማር ለመመስከር ወሰንኩ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ጊዜያት ተያያዥ ጥናቶችን ያቀረብኩ ቢኾንም ሀገራዊ በኾነ መንገድ በፊደል ዙሪያ ጥናት ያቀረብኩት የአፍ መፍቻ ቋንቋ በዓላት ሲከበሩ በትግራይ ክልል ሐውዜን ከተማ ፳፻፲፫ (በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር) ነው፡፡ በመቀጠልም በወልቂጤና በጂንካ ከተሞች በተመሳሳይ ኹኔታ በተከበሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በዓል ዝግጅቶች ላይ ከፊደል ጋር የተያያዙ ጥናቶች አቅርቤአለሁ (ሙሉጌታ፣ ፳፻፲፮)፡፡ በተለይ ሐውዜን ላይ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች የፊደል ገበታ ላቲን ወይስ ፊደል የሚል ጥናት አቅርቤ የታዳሚውን የፊደል ጥቅም ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ሞክሬአለሁ፡፡ ከበዓሉ ታዳሚዎች ውስጥ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚኾነው የኢትዮጵን ፊደል ማሳደግና ለሀገር በቀል ቋንቋዎች መጠቀም እንደሚገባ ተስማምቷል፡፡ እኛ ላቲንን መርጠናል የነፍጠኛውን ፊደል አንፈልግም ብለው የተቃወሙ ሁለት ተሳታፊዎች እንደ ነበሩም ትዝ ይለኛል፡፡ የመጡበትን ክልል መናገር አልፈለግኹም፡፡ የሚገርመው ግን ይህንን ጥናት በሐውዜን እንዳቀርብ ተጋብዤ ባቀርበውም መጀመሪያ ለማቅረብ ያዘጋጀሁት በዚያኑ ዓመት ባሕር ዳር በሚካሄደው ሀገር አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ ነበር፡፡ የቀረበው ጥናት ግን የፊደልን ጠቃሚነት አጉልቶ በማሳየቱና ብዙ ጥያቄዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ በማስነሣቱ በወቅቱ እንደ በጎ ሥራ

መወሰድ ስላልቻለ እንዳይቀርብ ታገደ፡፡ እኔም ሀገር በቀል ሀብታችንን እንጠቀም እናሳድግ ማለት የዚህ ዓይነት ምላሽ ሲሰጠው ኹኔታው ቢያሳዝነኝም ከጥናቴ ግን አልገታኝም፡፡ እኔም የሥነ ልሳን ባለሙያ በመኾኔ በተለይ በደቡብ በሚነገሩ ቋንቋዎች በማሌና በዲሜ ላይ ሰፊ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን ቀጠልኩ፡፡ የቋንቋዎቹን ንጽረ ድምፅ በመለየት በኢትዮጵያ ፊደል የቋንቋዎቹን ፊደል መቅረጽና መጠቀም ከላቲኑ የተሻለ መኾኑን በምርምር ሥራዎቼ አሳይቼአለሁ (ሙሉጌታ፣ ፳፻፲፮፤ ፳፻፳)፡፡ በአሁንም ወቅት አቡጊዳ በሚባል የፊደል ፕሮጀክት ላይ ከሙያ ጓዶቼ ጋር እየሠራሁ እገኛለሁ፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም የኢትዮጵያ ፊደል ለሀገር በቀል ቋንቋዎቻችን ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው፡፡

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ሀገር ከመኾኗ የተነሣ የራሷን ፊደልና የጽሑፍ ሥርዐት የምትጠቀም ሀገር ናት፡፡ የመጀመሪያው የጽሑፍ ሥርዐት ያለው ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ግእዝ ሲኾን ከዛ ቀጥሎ ፊደሎችን ከግእዙ በመዋስ የጽሑፍ ሥርዐት ኖሮት ለረጅም ጊዜ ያገለገለ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ደግሞ አማርኛ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የራሷን ማንነት ነጻነት አስከብራ ለቅኝ ግዞት ሳትንበረከክ ባህሏንና ቋንቋዋን ጠብቃ የኖረች ይልቁንም የጥንታዊው የግእዝ ቋንቋ ባለቤት የኾነች ብቸኛ ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ ታሪኳን ባህሏንና ሃይማኖቷን በራሷ ፊደልና ቋንቋ ስትዘግብ መኖሯ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ላይ ልዩ ሀገር ያደርጋታል፡፡ ግእዝንም ልዩ የሚያደርገው ከጥንታዊ ቋንቋዎች አንዱ መኾኑ ነው፡፡ ከታሪክ እንደምንረዳው መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸውና የተተረጎመባቸው ጥንታዊ ቋንቋዎች የሚባሉ አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አፍሪካዊ የኾኑት ግእዝና ቅብጥ ብቻ ናቸው፡፡ ግእዝ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ ሲኾን ቅብጥ ደግሞ የግብፅ ጥንታዊ ቋንቋ ነው፡፡ ምክረ ሥላሴ (፳፻፣ ገጽ ፱) እንደሚሉት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በመጀመሪያዎቹ ስድስት መቶ ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመባቸው በጣም ጥቂት የዓለም ቋንቋች መካከል ሁለቱ የአፍሪካ ቋንቋች እንደ ኾኑና እነርሱም ግእዝና ቅብጥ እንደ ኾኑ ይገልጻሉ፡፡ የግእዝን ቋንቋ ጥንታዊ ነው ብለው ካረጋገጡትና የግእዝን ሰዋሰው ወደ ላቲን በመተርጎም ከታወቁት ሊቃውንት አንዱ ጀርመናዊው ዲልማን ነው (ኑኅሚን፣ ፳፻፮፣ ገጽ ፩)፡፡

ኢትዮጵያ ለረዥም ዓመታት በአገልግሎት ላይ የዋለ የራሷ ፊደል ያላት በመኾኑ ይህንን አሳድጋና አበልጽጋ ሀገር በቀል ለኾኑት ቋንቋዎች መጠቀም ትችላለች፡፡ ከ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ በራሷ የጽሑፍ ዘዴ ስትጠቀም ኖራለች፡፡ የግእዝ ቋንቋ ከ፫፻፶ ዓ.ም. ጀምሮ በጣም አድጎና ጎልብቶ ብቸኛው ሀገራዊ ቋንቋ ኾኖ እስከ ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ አገልግሏል፡፡ ይኹንና ብዙ ሊቃውንት እንደሚሉት ግእዝ ጥንት አናባቢ ምልክቶች አልነበሩትም፡፡ አጻጻፋም ከቀኝ ወደ ግራ ነበር፡፡ ግእዝ አናባቢ ከግእዝ እስከ ሳብዕ እንዲኖረው፣ አጻጻፋም ከግራ ወደ ቀኝ እንዲኾን ያደረገው

በ0ራተኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረው አባ ፍሬምናጦስ ነው (ምክረ ሥላሴ፣ ፳፻፣ ገጽ ፭-፯)።

ኢትዮጵያ የራሷ ፊደልና የጽሑፍ ሥርዐት ስለ ነበራት የሀገሪቱ የታሪክ የቅርስ የትምህርት የፖለቲካና ልዩ ልዩ ሥነ ጥበባትና ባህሎች እንዲሁም የሃይማኖትና የጸሎት መጻሕፍት ሁሉ እየተዘገቡ ለትውልድ ሊተላለፉ ችለዋል። ስለዚህ ኢትዮጵያ የራሷን ፊደል በመጠቀም የዘመናት ልምድ አላት። የግእዝ ቋንቋ ኢትዮጵያዊ ፊደል ያለው የሥነ-ጽሑፍ ቋንቋ ኾኖ መገኘቱ ዛሬ ከግእዝ መጻሕፍት ወደ ብዙ ሀገራዊ ቋንቋዎች እየተረጎምን ለንባብ በማብቃት ለዕውቀት ሽግግር የሚጠቅሙ መጻሕፍት መኖር ዋና መሠረት አድርጎታል።

በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ አማርኛ በቤተ መንግሥትም ኾነ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ ሲመጣ ብሔራዊ ቋንቋ እየኾነ እንደ መጣ ሊቃውንቱ ይገልጻሉ (አየለ፣ ፲፱፻፺፯፣ ገጽ ፲፩)። አማርኛ በጽሑፉ እየተጠቀመ የቀጠለውም ይህንኑ ኢትዮጵያዊ ፊደል ነው።

በአሁኑ ወቅትም አማርኛ የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ ነው። በተጨማሪም የደቡብ ሕዝቦች፣ የጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የሥራ ቋንቋ ነው። ይህ ደግሞ የፊደል ተደራሽነቱ ሰፊ ያለ እንደ ኾነ ያሳያል። በመኾኑም ኢትዮጵያዊው ፊደል አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ እየተጠቀመበት ያለ፣ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሀብት የኾነ የጽሑፍ ሥርዐት ነው። በተለይ አሁን ሀገሪቱ ባወጣችው የቋንቋ ፖሊሲ መሠረት ወደ ፌደራል የሥራ ቋንቋነት እንዲያድጉ እየተሠራባቸው ያሉት ተጨማሪ ዐራት ቋንቋዎች የጋራ የኢትዮጵያ ፊደል መጠቀም ቢችሉ ኖሮ ምን ያህል ቋንቋዎቹን በጋራ ለመጠቀም እና የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ሌላውን ቋንቋ ለመማር፣ ለማወቅ እና ለማንበብ ይቀለው እንደ ነበረ መገመት አያዳግትም።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያን ፊደል አገልግሎት ለማጨናገፍ ለረጅም ዘመናት በተሠራ ተንኮል ብዙ የተጀመሩ ሥራዎች ቢሰናከሉም ብዙ የሀገሪቱ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ ፊደል መጠቀም ከጀመሩ ቆይተው ነበር። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ከመዛግብተ ቃላት ሥራና የመሠረተ ትምህርት (አፍ መፍቻ) ቋንቋ ጋር በተያያዘ በደርግ ዘመን ወደ ፲፫ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ ፊደል የየራሳቸውን የፊደል ገበታ ቀርፀው ወደ ትምህርት ገብተው ነበር። በተለይ የትግርኛ፣ የኦሮምኛ፣ የወላይትኛ፣ የሲዳምኛና የመሳሰሉት ቋንቋዎች በአትዮጵያ ፊደል ገበታ መሠረትነት የየራሳቸውን የፊደል ገበታ መሥርተው ወደ ሥራ ገብተው ነበር። ይኹንና አፍሪካውያን ከጥገኝነት ተላቀው በራሳቸው ሀብት መጠቀማቸው የእግር እሳት የኾነባቸው ምዕራባውያኑ በብዙ ስልትና ጥረት ጉዞውን

ለማደናቀፍ ሞክረዋል። ይህ ኾኖ ሳለም የኢትዮጵያን ፊደል እየተጠቀሙ የሚገኙ ከ፲፪ የማያንሱ የተለያዩ የቋንቋዎች ተናጋሪ ቤተሰቦች መኖራቸው ደግሞ አበረታች ነው። ይህም በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ለሁሉም ቋንቋዎች ማገልገል የሚችል ፊደል እንዳለን እንዱ ማረጋገጫ ነው። የበለጠ ከሠራን የኢትዮጵያን ፊደል ተጠቃሚነት ልናሰፋው እንችላለን። ሌላውን ለማወቅ ከመሮጥ ራሳችንን ከማወቅ ብንጀምር ሌላውንም አውቀን በአግባቡ ለመጠቀም ልምድም ግንዛቤም ይሰጠናል።

## ፩.፪ የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ለረዥም ዓመታት በአገልግሎት ላይ የዋለ የራሷ ፊደል ያላት በመኾኑ ይህንን አሳድጋና አበልጽጋ ሀገር በቀል ለኾኑት ቋንቋዎች መጠቀም እንደምትችል በሥነ-ልሳን ሳይንስና በፊደል ቀረጻ መርሖች ላይ ተመርኩዞ ማሳየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም ፊደል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ንጥረ ድምፅን የመወከል ብቃት ያለው መኾኑ፣ ፊደልን መጠቀም ሀገር በቀል ቋንቋዎችን ለመማርም ኾነ ለማስተማር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መኾኑ፣ ፊደል ለሀገራዊ አንድነትና የገጽ ግንባታ ከፍተኛ ሚና ያለው መኾኑን ማሳየት ነው።

## ፩.፫ የጥናቱ ዘዴና ንድፈ ሐሳብ

የኢትዮጵያን ፊደል ገበታ ጠቀሜታ ለመተንተን የተጠቀምነው ንድፈ ሐሳብም ስፐሯት (፳፻፪) የፈጠረው ኮምፒዩቴሽናል የጽሑፍ ዘዴ ንድፈ ሐሳብ ነው። በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሠረት ተገቢ ናቸው ተብለው የተጠቀሱ ሁለት ዐበይት ጉዳዮች አሉ። እነርሱም በሥርዐተ ጽሑፍ ውስጥ ወጥነትና ቀጣይ መደበኛነት ናቸው። ይህ ንድፈ ሐሳብ የትኛው የሥነ ልሳን ምልክት የጽሑፍን ፊደል ሊወክል ይችላል? በጽሑፍ ሥርዐትና በሚወከለው ድምፅ ምልክት መካካል ያለው ረቂቅ ፅንሰ ሐሳብ መካከል ምን ልዩነት ይኖራል? በጽሑፍ ሥርዐቱና በተወከለው የድምፅ ምልክት መካከል ምን ችግር ሊኖር ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልስልናል። ኮምፒዩቴሽናል የጽሑፍ ዘዴ ንድፈ ሐሳብ እንደ እነዚህ ያሉ ጉዳዮችን ማመስጠር መተንተን መተርጎም የሚያስችል ሳይንሳዊ መርሕ ነው። ለዚህ ጥናት የተጠቀምነው ተንታኝ የገለጻ ዘዴን ነው። የጥናቱን መረጃዎች ተመራማሪው ለፊደል ቀረጻ ወደ ማሌና፣ ሣላማጎ ወረዳዎች እንዲኹም በደቡብ ክልል ከተሰማራባቸው ሌሎች አካባቢዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ከሚናገሩ መረጃ ሰጪዎች የተሰባሰቡ መረጃዎች ናቸው። በተጨማሪም ከተለያዩ መጽሐፎችና የጽሑፍ መረጃዎች፣ ከማኅበራዊ ሚዲያዎች፣ ከተመራማሪው የዕለት ከዕለት ምልከታዎችና የመረጃ መረብ ወዘተ ለማሰባሰብ ተሞክሯል።

## ፪. በአፍሪካ የፊደል አጠቃቀም ሂደት አጭር ዳሰሳ

አፍሪካ በታሪክ ከዓለም አስቀድማ የጽሑፍ ሥርዐት የነበራት በራሷ ፊደል ትጠቀም የነበረች አህጉር ናት፡፡ ከዚህ በተቃራኒው የአውሮፓውያኑ ጥንታዊ ጽሑፍ የሚባለው የግሪኩ ጽሑፍ እ.ኤ.አ አስከ ፲፬፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጥቅም ላይ አልዋለም ነበር (ሌሳው ሞራዊኪ፣ ፳፻፪) እርሱም በአብዛኛው ከጥንታዊው የአፍሪካ ፊደል ፕሮቶ ሲናይቲክ (Proto-Sinaitic) የተቀዳ እንደ ኾነ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ጥንታዊ የአፍሪካ ፊደልና ጽሑፍ ከብዙ ዓመታት በፊት ጥቅም ላይ ውሎ እንደ ነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ (ባግሌሪ፣ ፳፻፬፤ ስቻማድ-ቤስራት፣ ፲፱፻፺፯)፡፡

ለአብነት ያህል ብናይ ፕሮቶ ሳሃራ (Proto Saharan (፶፻ - ፴፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት) የተባለውና በአርኪዮሎጂስቶችና የሥነ ልሳን ምሁራን የተሰየመው ቋንቋ የጽሑፍ ሥራዎቹ በተለያዩ የድንጋይ ቅርጻ ቅርጽ ላይ ተጽፈው እንደ ተገኙና ፊደሎቹም የኒሎቲክ ጣኦታትን የሚመስል ቅርጽ እንደ ነበራቸውና ከኑቢያ ምዕራብ አቅጣጫ እንደ ተገኘ ይነገራል፡፡ የዚህ ቋንቋ ፊደላት አሁን አፍሪካ እየተጠቀመችባቸው ካሉት ቲፊናሕ (Tifinagh) እና ቫይ (Vai) ጋር እንደ ሚመሳሰሉ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ቫይ (Vai) ፊደል ከክርስቶስ ልደት በፊት (፶፻ - ፴፻) ጥቅም ላይ ውሎ ነበር ከሚባለው ከጥንታዊው ፕሮቶ ሳሃራ ፊደል ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንደ ኾነ ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡ ይህ ፊደል በዓለም ጥንታዊ ከሚባሉት ፊደሎች አንዱ ሲኾን አሁን በላይቤሪያ እና በሴራሊዮን ጥቅም ላይ ያለ አፍሪካዊና ቀለማዊ (syllabary) የኾነ ፪፻፲ የሚደርሱ ምልክቶች ያሉት የጽሑፍ ዓይነት ነው (ዳልቢ፣ ፲፱፻፷፯፣ ገጽ ፩—፶፩).

ቲፋናሕ (Tifanagh) አሁንም በጥቅም ላይ ያለ ፊደል ነው፡፡ በተለይ በምዕራብ አፍሪካ በበርካታ ቦታዎች ይነገራል ማሊን ኒጀርን፣ ቻድን ቡረኪናፋሶን፣ ደቡብ አልጀሪያን እና ደቡብ ሊቢያን ጨምሮ፣ ታማዛይት (Tamazight) ቡድን ተብለው የሚታወቁ ሲኾን የሚጠቀሙት ይህንኑ ፊደል ነው፡፡ በአሁኑ ግዜም ብዛት ያላቸው ታማዛይት ተናጋሪ የሚባሉት ይህንኑ ፊደል በራሳቸው መንገድ ወስደው እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ ጠቅለል አድርገን ስናየው አፍሪካ በቀል የጽሑፍ ሥርዐት ያላቸው እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል (ሚሊዮን፣ ፳፻፰፣ ገጽ ፬፤ አንደርሰን፣ ፳፻፲)፡፡

*ሰንጠረዥ -፩ አፍሪካ በቀል የጽሑፍ ሥርዐት ያላቸው ሀገራት (ከMafundikwa, ፳፻ የተወሰደ)*

| No. | **የጽሑፍ ሥርዐት** | **የተገኘበት ሀገር** | ጥቅም ላይ መዋል የጀመረበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ፩ | የግብፅ የጽሑፍ ሥርዐት | ግብፅ | ፴፬፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| ፪ | የኢትዮጵያ ፊደል | ኢትዮጵያ | ፳፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| ፫ | የቫይ (Vai) ፊደል | ምዕራብ አፍሪካ | ፴፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| ፬ | የባሳ (Bassa) ፊደል | ላይቤሪያ | ፲፱፻፳ ዓ.ም. |
| ፭ | የሜንዴ (Mende) ፊደል | ሴራሊዮን | ፫፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| ፮ | የሲ.ቢ.ዲ/ሲ.ቢ.ሪ (Nsibidi/ Nisibiri ) ፊደል | ናይጀሪያ እና ካሜሩን | ፫፻ ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| ፯ | የሹሞም (Shumom) ፊደል | ካሜሩን | |
| ፰ | የሜርዮቲክ (Meriotic ) ፊደል | ሱዳን | |

ከዚህ በላይ ረዥም እድሜ ያላቸው አፍሪካዊ ፊደላትንና የኢትዮጵያን ፊደላት ጥንታዊነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ነው፡፡ ፓስች (፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፩) እንደ ጠቀሰው ብዙ የአፍሪካ ሀገር በቀል ፊደሎች እየጠፉ በላቲን እንደ ተተኩ ያሳያል፡፡ ኢልገሃሚስ ረመዳን (፳፻፲) ሌይደን ኔዘርላንድ በጻፈው የፒ.ኤች.ዲ መጽሐፉ እነዚህ እንደ ቲፋናሕ (Tifanagh) ያሉ ጥንታዊ አፍሪካዊ ፊደላት በአብዛኛው በቱዋሬግ ኅብረተሰብ ዘንድ በደቡብ አልጀሪያ፣ ኒጀር፣ ማሊና፣ ቡረኪናፋሶ አገልግሎት እንደሚሰጡ ጠቅሷል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የኢትዮጵያን ፊደል የትመጣ እናያለን፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ እንደሚገኙ ብዙ ሀገራት ልሳነ ብዙ ናት፡፡ ነገር ግን ከሌሎቹ የአፍሪካ ሀገሮች በእጅጉ ትለያለች፡፡ ይኸውም በቅኝ ግዛት ሥር ሳትወድቅ በነጻነት የኖረች ሀገር በመኾኗ ቅኝ ግዛት ጥሎባት የሔደው የቋንቋና የባህል ወረራ አሻራ የላትም፡፡ በፊደሏም ለረዥም ዘመናት ያለምንም ተጽእኖ ስትጠቀም ኖራለች፡፡ ነገር ግን የአፍሪካ ሀገራት ሀገር በቀል ቋንቋ መርጦ የጋራ መግባቢያ ለማድረግ በፊደሉም ለመጠቀም ከቅኝ ገዢዎቻቸው የወረሷቸው ሰፋፊ ችግሮች አሉባቸው፡፡ ኾኖም ያሉባቸውን ችግሮች አልፈው የራሳቸውን ፊደልና ቋንቋ ለመጠቀም ሲጥሩና

ሲታገሉ እናያለን። ኢትዮጵያችን ከቅኝ ግዛት ዳፋ አምልጣለች ብንልም በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የራሷን ፊደል ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም እንዳትችል የሚያደርግ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ችግር ገጥሟታል። *"የቅኝ ግዢ ዘመን ካለፈ ሁለት ትውልድ ያለፈው ቢኾንም የቅኝ ግዢ አሠራር ግን በርግጠኛነት ገና አልተወገደም"* (ኢሪንግተን፣ ፲፱፻፹: ገጽ ፩) እንዳለው ዮሴፍ ኢሪንግተን በአፍሪካም ኾነ በኢትዮጵያ ዛሬም የኮሎኒያሊዝም ፈተና በእጅ አዙርም ኾነ በልዩ ልዩ ስልት አሻራው በቋንቋ በባህልና በማንነት ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖውን የሚያመላክቱ ብዙ ምልክቶች አሉ። ለዚህም በኢትዮጵያዊ ፊደል ላይ የደረሰው ፈተና አንዱ መገለጫ ነው። ለኢትዮጵያ ፊደል እድገት መነሻ ነው የሚባለውን የሳቢያን ፊደል ቀጥሎ እንመለከታለን (መሸሻ እና ጀዋር ፲፱፻፹፡ገጽ ፹)

*ሰንጠረዥ -፪: የሳቢያን ፊደል*

ከሳቢያን ፊደል ግእዝ እንዴት በራሱ መንገድ ፊደላትን እንደ ተጠቀመ ያሳያል።

*ሰንጠረዥ -፫: የፊደል አጀማመር*



ከዚህ ከቀረበው ሰንጠረዥ የምንረዳው ግእዝ የሳባ ፊደልን ቀጥታ የወሰደ ሳይኾን ለራሱ በሚጠቅመው መንገድ እያሻሻለ እየለወጠ መጠቀሙን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፊደል አሠራርና አፈጣጠር የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የፈጠራና የፍልስፍና ጥበብም የተንጸባረቀበት ነው፡፡ እንደውም አንዳንድ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የግእዝ ፊደል ከጥንት ከካም ዘመን ጀምሮ የነበረ እንደ ኾነ በማስረገጥ ከሳባ ፊደላት የመጣ ነው የሚለውን ይቃወማሉ፡፡

ከካም ዘመን ጀምሮ እስከ ፵፰ ዓ.ም ዘመን ድረስ የቆየውን ታሪክ ለመደምሰስ ታስቦ በኢትዮጵያ ፊደልን ያመጡ የደቡብ ዐረቦች ግእዝን አመጡ ያንንም አባ ሰላማ ከካእብ እስከ ሳብዕ ያሉትን የፊደል ደረጃዎች አሰናዳ፤ መጻሕፍተ ብሉያትም በአባ ሰላማ ከጽርዕ ወደ ግብፅ ተገለበጡ ይላሉ፡፡ መጻሕፍተ ብሉያት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን በጭራሽ የካዱ ይህንንም የተሳሳተ ትምህርት ያጠኑ ሰዎች በርክተዋል፡፡ …ከካም ጀምሮ መንግሥቱና ፊደሉ ቋንቋው እንደ መጣ እናስተውል (አስረስ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፩-፳፮)፡፡

*ሰንጠረዥ-፬፡ የፊደል እድገት*




ስለ ፊደል የትመጣ በጥልቅ ለመረዳት ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ፊደል ከካምም ከሳባም አልመጣም መነሻውም መፈጠሪያውም እዚሁ ኢትዮጵያ ነው ብሎ መነሣትም ይቻላል፡፡ኾኖም በመረጃ የተደገፈ የምርምር ሥራ ይጠይቃል፡፡ በማንኛውም መንገድ ሲታይ ፊደል የራሱ የኾነ የእድገት ሂደት እንደ ነበረው እንገነዘባለን፡፡ የፊደልን እደገት በመጠኑ ለማየት የተወሰኑ ምሳሌዎችን ቀጥሎ እንመልከት (ጋብሬላ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፬)፡፡

ፊደል በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በግምት ከ፳፫፻ ዓመት በፊት ከደቡብ ዐረቢያ ከመጡ የሴማውያን ቤተሰብና የሳቢያን ቋንቋ እየተቃና የተወሰደ መኾኑ ይነገራል (ገ/መስቀልና አበራ፣ ፳፻፳፣ ገጽ ፫)፡፡ የኢትዮጵያ ፊደል ከጥንታዊው ግብፅና የሌሎችም ጥንታዊ

ቋንቋዎች ፊደል ጋር እንደሚመሳሰል እና ቀስ በቀስም የራሱን ቅርጽ እየያዘ እንዳደገ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

*ሰንጠረዥ -፫፡ የፊደላት ቀስ በቀስ እድገት ከገብሬላ (፳፻፩:፬)*

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው የጽሑፍ ፊደላት ቀስ በቀስ ከሥዕላዊ (logographic) ወደ ሲላባሪክ ከዚያም ወደ አልፋቤት እንደ ተለወጡ ነው፡፡

በሥነ ልሳን ሙያ እንደምንረዳው ቋንቋ ይወለዳል ያድጋል ይሞታል፡፡ ይሄ ከታሪክም የምንማረውና የምናረጋግጠው እውነታ ነው፡፡ ፊደልም የቋንቋ መገለጫ መሣሪያ በመኾኑ የሚፈጠር የሚያድግ እንደ አስፈላጊነቱ ሊኖር ወይም ሊጠፋ የሚችል ነገር ነው፡፡ ፍቅሬ (፳፻፤ ገጽ ፱) እንደሚገልጹትም ኾነ ከተለያዩ የጽሑፍ መረጃዎች እንደምናነበው የግእዝ ፊደል፣ የተፈጠረበት ያደገበት እና አሁን ያለበት ደረጃ የደረሰበት የራሱ የኾነ ሰፊ ታሪክ አለው፡፡ ሊቃውንት ብዙ ተፈላስፈውበታል፣ በየጊዜው እንደ አስፈላጊነቱ አሻሽለውታል (አእምሮ፣ ፳፻፣ ገጽ ፶)፡፡ ግእዝ ከሳባውያኑ ፊደል የወሰደው አለው፤ ከጥንታውያን የግሪክና የመሳሰሉ ቋንቋዎች ጠቃሚ የኾኑ ነገሮችን በመውሰድ ከቀኝ ወደ ግራ የነበረው ከግራ ወደ ቀኝ የአጻጻፍ አቅጣጫ ይዟል፡፡ ስለዚህ አንዳንዶች በልምድ እንደሚጠሩት የኢትዮጵያ ፊደል የሳባ ፊደል ተብሎ ሊጠራ አይገባም፡፡ አንድ ፊደል መነሻው እንደ ታሪክ ቢጠቀስም የተደረሰበት ግኝቱ ነው ስም ሊሰጠው

የሚገባው፡፡ የኢትዮጵያ ፊደል የሳባ መነሻነት ቢኖረውም አሁን የብዙዎች ቋንቋዎች ፊደል በመኾኑ የሳባን ፊደል መነሻ አድርጎ እያሻሻለ ብዙዎቹን በሚጠቅሙት መንገድ እየቀረጸና ፊደላትን ፈልጎ እያሟላ ያደገ በመኾኑ የኢትዮጵያ እንጂ የሳባ ፊደል ሊባል አይገባም። የግእዝ ፊደል ጥንታዊና ኢትዮጵያዊ በመኾኑ በሀገሪቱ ውስጥ ላሉ ሁሉም ብሔር ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሀብት መኾኑን ልንረዳው ያስፈልጋል። በታሪክ እንደሚታወቀው ይህ የላቲን የጽሑፍ ዘዴ በመካከለኛው ምሥራቅ የሴሜቲክ ቋንቋዎች ከሚጠቀሙበት የሲላባሪ (ቀለም) ዘዴ የተወሰደ በአብዛኛው በግሪክ ይታወቅ ስለ ነበረ የግሪክ አልፋ ቤት ተብሎ የሚነገር በኋላ ሮማውያኖቹ ከግሪክ ወስደው የራሳቸው አድርገው አሻሽለው በመጠቀም በቅኝ ግዢ በያዙአቸው ሀገሮች ያስፋፉት የጽሑፍ ዘዴ ነው ( ጎርዶን፣፲፱፻፺፯)፡፡ ኢትዮጵያ ግን በቅኝ ግዢ ከወደቁ የአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ ተለይታ ኢትዮጵያዊ የኾነ የግእዝ ፊደልን በቀለማዊ የጽሑፍ ዘዴ በመጠቀም የራሷ ፊደል ያላት አፍሪካዊ ሀገር ለመኾን በቅታለች፡፡ ይህንን የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾን የአፍሪካውያን ሀብት የኾነ ፊደላችንን ልናሳድገውና የአገልግሎት አድማሱንም አህጉራዊ በማድረግ ሲገባ እንደ ዋዛ በምዕራባውያኑ ተጽእኖ ሥር ወድቀን ልናጣጥለው አይገባም፡፡

## ፫. ኢትዮጵያዊ ፊደልና አገልግሎቱ በዘመናችን

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሀገር እንደ መኾኗ ወደ ፹ የሚደርሱ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ሀገር ናት፡፡ ሀገሪቱ በምታከናውናቸው የቋንቋ ልማት እንቅስቃሴዎች ወደ ፶፪ የሚደርሱት ቋንቋዎች የጽሑፍ ዘዴ የተዘጋጀላቸው ሲኾን የተቀሩት ቋንቋዎች ግን ለዚህ ዕድል ገና ያልበቁ ናቸው፡፡ በነዚሁ ጅምር ሥራዎችም ላይ እንኳ እንደሚታየው በፊደል ገበታ ዝግጅት ሥራ በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ድምፆች በተገቢው መንገድ በመቅረጹ ረገድ ብዙ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የራሳችንን ጥለን ወደ ላቲኑ ከመሄድ ይልቅ ኢትዮጵያዊ የኾነውን ፊደልና የፊደል ገበታ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብንጠቀም በሚለው ሐሳብ ላይም ሰፊ የኾነ ችግሮችና የግንዛቤ ክፍተት አለ፡፡

> በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ በራሱ ቋንቋ የመናገር የመጻፍና ቋንቋን የማሳደግ ባህሉን የመግለጽ የማሳደግ የማሳወቅና ታሪኩን የመጠበቅ መብት አለው” (አንቀጽ ፴፱ የዜግነት መብት)፡፡

እያንዳንዱ ኅብረተሰብ በራሱ ቋንቋ እንዲናገር ቋንቋውን እንዲያሳድግ ባህሉንና ታሪኩን እንዲዘግብ ሕገ መንግሥቱ መብት ሲሰጠው ብሔራዊ ሀብቱንና ማንነቱንም ጠብቆና አስጠብቆም ማደግ እንዳለበት አቅጣጫ አላስቀመጠለትም፡፡ ይሄ በሕገ መንግሥቱ

ላይ ያለ ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለ ሀገራዊ ሀብቱና ማንነቱ ቆም ብሎ ማሰብ ይኖርበታል፡፡ የሀገሪቱ ቋንቋዎች ወደ ጽሑፍ ሲያድጉ የሀገራቸውን ፊደል ለቋንቋቸው እድገት እየተጠቀሙ ቢኾን ብሔራዊ አንድነታቸውን የበለጠ ያጎላዋል፤ ትልቅ የማንነት አሻራም ይኖረዋል የሚል ጠንካራ አስተያየት የሚሰጡ አሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የኢትዮጵያ ፊደል የሀገር ቅርስ ሀብት ማንነት ወዘተ የሚሉት አባባሎች ከቁብም የማይቆጥሩት ስለ ሀገር በቀል ቋንቋና ፊደል ማንሣትን እንደ ኋላ ቀርነት የሚቆጥሩትም አሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ረገድ ያለውን አመለካከት በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ በተለያዩ ምሁራን የሚሰጡትን ሐሳቦች እንደሚከተለው ዘርዘር አድርገን እንያቸው፤

፩. ሁሉም የሀገሪቱ ቋንቋዎች የግእዙን ፊደል ሙሉ በሙሉ ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ ተጠቅመው ወደ ጽሑፍ ማደግ ይችላሉ

፪. ሁሉም የሀገሪቱ ቋንቋዎች የግእዙን ፊደል መሠረት አድርገው የየራሳቸው ንጥረ ድምፅ ላይ መሠረት ያደረገ የየራሳቸውን የፊደል ገበታ መሥርተው ወደ ጽሑፍ ማደግ ይችላሉ

፫ የሴማውያን ቤተሰቦች የግእዙን ፊደል መሠረት አድርገው የየራሳቸውን ንጥረ ድምፅ መመሥረት ይችላሉ ሌሎቹ የኩሻውያን፣ የኦሞያውያን፣ የናይሎ ሳሃራውያን ግን የግእዙ ፊደል በውስጣቸው ያለውን ንጥረ ድምፅ ሊወክል ስለማይችል ላቲን መጠቀም አለባቸው የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሐሳቦች ዘርዘር አድርገን ስንመለከት ሁሉም የኢትዮጵያ ፊደል የምንለውን የግእዝ ፊደል መጠቀም እንዳለብን ይስማማሉ፡፡ ልዩነቱ ያለው አጠቃቀማችን እንዴት እና እስከ ምን ድረስ የሚለው ላይ ነው፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተቀመጠው ሐሳብ ብዙ ጊዜ የሚነሣው የግእዝ ዕውቀት ያላቸውና የሌሎቹንም ቋንቋዎች ንጽረ ድምፅ በግእዙ መነጽር ለማየት የሚሞክሩ ሊቃውንት ናቸው፡፡ በሥነ ልሳን ትምህርት እንደምንረዳው እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ የኾነ ንጥረ ድምፅ አለው፡፡ ስለዚህ የራሱ የኾነ የፊደል ገበታ ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ ግእዝ የራሱ የኾነ ንጥረ ድምፅ አለው፤ የራሱ የኾነ የፊደል ገበታም አለው፡፡ የንጽረ ድምፅ አጠቃቀሙም የራሱ ሕግ አለው፡፡ ስለዚህ ይህንን የንጽረ ድምፅ አጠቃቀም ማንም ሰው ተነሥቶ በፈለገው መንገድ ሊቀይረው አይችልም የቋንቋው ባሕርይ ነውና፡፡ የግእዝ ፊደል ቅርጽ መለያየት የድምፁ መመሳሰልና መለያየት የራሱ የኾነ ታሪካዊ ሂደት አለው፡፡ የአንድ ቋንቋ ንጥረ ድምፅ በዓይነትም በብዛትም ስለሚለያይ

የግእዙን እንዳለ ወስዶ ለሌላው ቋንቋ ማድረግ በቋንቋ አጠቃቀሙ ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ የአማርኛ ፊደል ሲቀረጽ በአብዛኛው በራሱ ንጥረ ድምፅ ላይ መሠረት አድርጎ ስላይደለና የግእዙን እንዳለ በመውሰድ ስለ ነበረ ከአማርኛው ፊደል ተደጋጋሚ የተባሉትን መቀነስ ልክ የግእዝ ፊደሉንም መቀነስ ተደርጎ ስለ ተወሰደ የፊደላት መቀነስ አለመቀነስ ጉዳይ ለረዥም ዘመናት ሲያወዛግብ የኖረ ነው። ለአማርኛ ፊደል የቀረፁት የግእዝ ሊቃውንት የአማርኛውን ንጥረ ድምፅ በአማርኛው መነጽር ሳይኾን በግእዙ መነጽር ስላዩት ነበረ፡፡ አንድም በግእዙ ያሉና ለአማርኛው የማያስፈልጉ ፊደሎችን ከአማርኛው ፊደል ገበታ ማስወገድ የፊደሉን ቅርስና ሀብትነት እንደ ማጥፋት ስለ ቆጠሩት ሁሉም ጓዝ በአማርኛውም ተካቶ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ይሄ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ግእዝ የማያውቅ ትውልድ ሲመጣ በአማርኛ ውስጥ የግእዙን የፊደል ጓዝ በሙሉ ይዞ መቀጠል ከበደው፤ አወዛገበው፡፡ በአማርኛ ፊደል ቀረጻ ሂደት ውስጥ የግእዙን ፊደላት እንዳለ ወስደው ከግእዙ ውስጥ የሌሉትን ብቻ ነው በአዲስ ድምፆች ለመወከል የተሞከረው፡፡ በግእዙ ውስጥ ያሉት ፊደላት (ሀ ሐ ኀ) ፣(ሰ ሠ )፣ (ጸ ፀ) እና (ዐ አ) ለአማርኛው በሚመጥን መልክ ተመርጠው መወሰድ ነበረባቸው። ይህ ዓይነቱ ችግር በሌሎች ቋንቋዎች መደገም የለበትም። አንዳንድ ምሁራን ፊደል ይቀነስ አይቀነስ የሚለው ክርክር በአማርኛው የፊደል ገበታ ላይ ብቻ መሠረት ያደረገ ሳይኾን የግእዙንም የሚመለከት እየመሰላቸው የግእዙን ጠቅሰው ሲከራከሩ ይታያል። ወደፊት እንደዚህ ያለ ችግር እንዳይፈጠር ሁሉም ቋንቋ የግእዙን ፊደል መሠረት አድርጎ የራሱን ንጥረ ድምፅ መመሥረት አለበት፡፡

በሁለተኛው ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ሁሉም የሀገሪቱ ቋንቋዎች የግእዙን ፊደል መሠረት አድርገው በየራሳቸው ንጥረ ድምፅ ላይ መሠረት ያደረገ ኢትዮጵያዊ የኾነ የየራሳቸው የፊደል ገበታ መሥርተው ወደ ጽሑፍ ማደግ ይችላሉ የሚለው ሐሳብ በሥነ ልሳን ሳይንስ ተቀባይነት ያለው ሐሳብ ነው። ተጠቃሚው የራሴ ብሎ እስከ ተስማማ ድረስ ማንኛውም የፊደል ገበታ ለማንኛውም ቋንቋ አስፈላጊው የንጽረ ድምፅ ማስተካካያ እየተደረገለት ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ አውሮፓውያን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ለየቋንቋዎቻቸው የሚጠቀሙት የላቲኑን ፊደልን መሠረት አድርገው ነው፡፡ ላቲን ሀብታችን ቅርሳችን ነው ብለው ስለሚያምኑ፡፡ ለምሳሌ ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ ወዘተ የሚጠቀሙት የላቲን ፊደልን መሠረት አድርገው ነው፡፡ እነርሱ ግን እኛን የሚመክሩን የሚገፉን እነርሱ የራሳችን ብለው ላቲንን እንደ ተጠቀሙት ሁሉ እኛም የራሳችን ብለን የግእዝ ፊደል እድንጠቀም ሳይኾን የእኛን ጥለን የእነርሱን ላቲንን የእኛ አድርገን እድንጠቀም ነው፡፡ የራሳቸውን እየተጠቀሙና እያሳደጉ የእኛን በማጣጣል ወደ እነርሱ ጥገኛ ለማድረግ ይጥራሉ፡፡

በኤሽያ ያለውንም በተመሳሳይ ብናይ ቻይና ጃፓን የሚጠቀሙት የየራሳቸውን ፊደል ነው።

በሦስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው የሴማውያን ቤተሰቦች የግእዙን ፊደል መሠረት አድርገው የየራሳቸውን ንጥረ ድምፅ መመሥረት ይችላሉ። ሌሎቹ የኩሻውያን፣ የኦሞያዊያን፣ የናይሎ ሳሃራውያን ግን የግእዙ ፊደል በውስጣቸው ያለውን ንጥረ ድምፅ ሊወክል ስለማይችል ላቲን መጠቀም አለባቸው የሚለው ሐሳብ ሥነ ልሳናዊ መሠረት የሌለው በመኾኑ አብዛኞቹ ፊደላቸውን እየተጠቀሙበት ስለ ኾነ ሙሉ በሙሉ ባናስጥላቸው እንኳን ቢያንስ የተወሰኑትን እንኳ ምክንያት ፈጥረን ወደ እኛ እንውሰዳቸው ላቲኑ እየተለመደ ሲመጣ ሌሎቹን ቀስ በቀስ ለመጠቅለል እንሞክራለን የሚል አንድምታ ያለው ሐሳብ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ይመስላል። በአፍሪካ በቅኝ ግዢ ዘመናት የተደረጉት ተግባራት ይህንን የሚያረጋግጡ ናቸው።

ስለዚህ በጥንቃቄ ሰፋ አድርገን ማሰብ ያለብን ጉዳይ ለፊደላችን የሚገባውን ክብርና ቦታ መስጠት ነው። ይህን ማድረግ እስከ ቻልን ድረስ ሁሉም ብሔር ብሔረሰብ ቋንቋውንና ባህሉን እያሳደገ በራሱ ቋንቋ እየተጠቀመ በድምሩ ደግሞ የሀገሩን ታሪክና ቅርስ የማንነቱን አሻራ ጠብቆ መንቀሳቀሱ ለብሔራዊ ክብሩና አንድነቱ የተሻለ እድል እንደሚሰጥ ማጤን ይገባል። "ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅመኝም" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ የበለጠ ጠቃሚ የኾነው ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ መልካም ነው። "ሁሉን እዩ መልካሙን ግን ያዙ" ያለውን መከተሉ ይጠቅመናል እንጂ ጉዳት የለውም።

በመኾኑም ቀድመው በታሪክ አጋጣሚ ወደ ጽሑፍ ያደጉ እንደ ግእዝና አማርኛ እንዲሁም በቅርቡ ኢትዮጵያዊውን ፊደል እየተጠቀሙ እንዳሉት ፲፪ የሚደርሱ ቋንቋዎች ሁሉ ሌሎችም የሀገራችን ቋንቋዎች ሀገር በቀል የኾነውን ኢትዮጵያዊ ፊደል እንደየ ቋንቋዎቹ የድምፅ ባሕርይ ኹኔታ አስማምቶ በመጠቀም ሁሉም ቋንቋቸውን ወደ ጽሑፍ በማሳደግ ቢሠሩ የበለጠ ጠቃሚ መኾኑን በዚህ ጽሑፍ ለማሳየት እንሞክራለን። ኢትዮጵያዊውን ፊደል ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጠቀም እንደሚገባ ሰፊ ሥራ የሠሩ ምሁራንን ሥራ ከግምት አስገብተን እናያለን (ባየ፣ ፲፱፻፹፬፤ ፍቅሬ፣ ፳፻፩፤ ሙሉጌታ፣ ፳፻፳፤ ፳፻፲፯)።

*ሰንጠረዥ -፯ የኢትዮጵያ ፊደል ለጽሑፍ የሚጠቀሙ ቋንቋዎች*

| ተ.ቁ | የሴም | የዓባይ ሰሀራዊ | የኦሞ | የኩሽ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | አማርኛ | ኩናማ | ባስኬቶ | ኢሮብ(ሳሆ) |
| ፪ | ትግሪኛ | | | ኣዊንጊ |
| ፫ | አርጎባ | | | ኽምጣንኛ |
| ፬ | ሀረሪ | | | ቀቤና |
| ፭ | ስልጤ | | ማሌ | |
| ድምር | ፭ | ፩ | ፪ | ፬ = ፲፪ |

## ፬. የፊደል ቀረጻ መሠረታዊ ሐሳቦች

ስለ ፊደል ቀረጻ ስናነሣ በዓለም ላይ ሦስት ዓይነት የጽሑፍ ዘዴዎች እንዳሉ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ባየ (፲፱፻፹፬) እንደ ጠቀሰው ዋና ዋናዎቹ ሦስት ዓይነት ናቸው፡፡ እነርሱም ሎጎግራፊክ (logographic)፣ የቀለም ወይም ሲላባሪክ (syllabarry) እና አልፋቤቲክ (alphabetic)፡፡ ሎጎግራፊክ የሚባለው በጣም ጥንታዊና ከ፵፻ ዓመታ በፊት በፓሊስቲንና በሲሪያ አካባቢ የተጀመረ እንደ ነበረ ይነገራል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ዘዴ አንድ ምልክት አንድ ቃል ይወክላል፡፡ ጥንታዊው የቻይና ፊደል ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የሁለተኛውን ዘዴ ስንመለከት የሲላባሪ ወይም የቀለም የጽሑፍ ዘዴ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ዘዴ አንድ ምልክት የሚወክለው ድምፅን ሳይኾን ፊደልን ነው፡፡ ይህም ማለት የአናባቢንና ተናባቢ ድምፅን አንድ ላይ አጣምሮ መያዝ ማለት ነው፡፡ ለአብነትም ያህል የኢትዮጵያ ፊደል ሲላባሪክ ነው፡፡ ሌላው የአልፋቤቲክ የጽሑፍ ዘዴ የሚባለው ነው፡፡ እርሱም ተናባቢንና አናባቢን ድምፅ ለየብቻው የሚወክል ምልክት ያለው የጽሑፍ ዘዴ ነው፤ ለዚህ ደግሞ እንግሊዝኛ እና ላቲን ምሳሌ ይኾናሉ፡፡

ማንኛውም ፊደል ለማንኛውም ቋንቋ የተወሰነ ማስተካከያ እስከ ተደረገለት ድረስ ማገልገል ይችላል፡፡ አዲስ ፊደል ቀርጾ ወይም ካሉት ፊደላት መርጦ የተሻለውን መጠቀምም የተለመደ አሠራር ነው፡፡ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ለማሳየት እንደ ተሞከረው በፊደል ቀረጻ ውስጥ የሥነ ድምፅ፣ የሥነ ምዕላድ፣ የባህልና ማንነት፣ የታሪክና የቅርስ፣ የፖለቲካና ጂኦግራፊ፣ የሥነ ልቡናና እና ሥነ ልሳን እንዲሁም ማኅበራዊ ሥነ ልሳን ከግምት ውስጥ ሊገቡና ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

*ሰንጠረዥ -፰: በፊደል ቀረጻ ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች*




አንድን ቋንቋ ወደ ጽሑፍ ደረጃ ማሳደግ ቀላል ነገር አይደለም:: ከሥነ-ልሳን፣ ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከማኅበራዊና ከፖለቲካዊ ኹኔታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለረጅም ዘመን በንግግር ብቻ ተወስኖ በውስጡ ያቆየውን የቋንቋውን ልዩ ባሕርይ በሚያሳይና ሳይንሳዊ በኾነ መልኩ ቋንቋው የጽሑፍ ሥርዓት እንዲኖረው ለማድረግ ከፍተኛ ዝግጅትና ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡ ለአንድ ቋንቋ ጽሑፍ ስናዘጋጅ የሥነ ልሳን ጥናትና በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የባለሙያው ተሳትፎ በቋንቋው ውስጥ ያሉት ድምፆች በትክክል እንዲካተቱ፣ የቋንቋ የሰዋሰው አወቃቀር በትክክል እንዲካተት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ ነገር ግን ይህን እውነታ ብቻ ይዘን ፊደል መቅረጽ አንችልም፡፡ የፊደል ቀረጻ ከላይ እንደ ጠቀስነው ከብዙ ኹኔታዎች ጋር የተያያዘ ስለሚኾን በሥራው ውስጥ ሊታሰቡና ትልቅ ቦታ ሊኖራቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም ከላይ በግራፉ ላይ ለማሳየት እንደ ተሞከረው የማኅበረሰቡ ሥነ ልቡና፣ ባህልና ማንነት፣ ሥነ ምድራዊና ፖለቲካዊ ኹኔታ፣ ቅርስና ታሪካዊ ኹኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

በፊደል ቀረጻ ሂደት ውስጥ ብዙ ፈተናዎች/ችግሮች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

*ሰንጠረዥ -፫: የፊደል ቀረጻ ተግዳሮቶች*

በአንድ ፊደል ቀረጻ ሂደት ውስጥ ታሳቢ የሚኾኑና አስቸጋሪ ሊኾኑ የሚችሉ ጉዳዮች በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል። እነዚህ ሁሉ ለአንድ ቋንቋ የጽሑፍ ዘዴ ለመፍጠርና የተዋጣለት ፊደል ለመቅረጽ ወሳኝ ኹኔታዎች ናቸው። የራስን እድል በራስ ለመጠቀም የሌሎችን ጣልቃ ገብነት መመከት ዋነኛ ተግባር ሊኾን ይገባል። የሌሎችን ጣልቃ ገብነት መመከት እንዲገባ ሮይ የጠቀሰውን ማየት ይጠቅማል (ሮይ-ካምፕቤል፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፬)።

በመኾኑም አፍሪካውያን የሌላውን ሁሌ ተቀባይ መኾን እንደሌለባቸው ከተቀበሉም የሚጠቅማቸውን ብቻ መርጠው መውሰድ እንዳለባቸው አለበለዚያ አፍሪካውያን ቋንቋዎች በትምህርትና በሳይንስ ያላቸው ጠቀሜታ ዝቅተኛ እንደሚኾን ለዚህም አፍሪካውያን አቋማችንን ማስተካከል እንደሚገባ ይጠቁማል (ሮይ-ካምፕቤል፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፫)። እኛ ኢትዮጵያውያንም ከተቀባይነት ወደ ሰጪነት ከሰው አድናቂነት ወደ ራሳችን አድናቂነት መሸጋገር አለመቻላችን ብዙ ነገሮቻችን ላይ የሌሎች ተጽእኖ ላይ ለመውደቅ ዳርጎናል። ኢትዮጵያ ያላትን ጥንታዊ ፊደል ተጠቅማ ሀገር በቀል ቋንቋዎቿን በራሷ ፊደል ማሳደግ ለራሷም ብቻ ሳይኾን ለአፍሪካ ቋንቋዎችም እድገት በፊደሎቿ አስተዋጽኦ ማድረግ ሲገባት ሁል ግዜ ተቀባይ እንጂ ሰጪ እንዳትኾን፣ የሌላውን አድናቂ እንጂ ለራሷ ሀብትና ቅርስ የማይገዳት እንድትኾን እኛን በጥቃቅን ነገሮች እየለያዩ ለልዩነታችንም የእነርሱ የኾነ ነገር ብቻ መፍትሔና አስታራቂ አድርገው በማቅረብ በአፍሪካውያን ኀሊና ይጫወቱብናል።

ስለዚህ የሁሉም ምርጫና አጠቃቀም ደግሞ እንደ ሀገር ስናስብ ለታሪካችን፣ ለአንድነታችን፣ ለማንነታችንና ለጋራ ጥቅማችን በሚበጁን ኹኔታዎች ላይ ትኩረት በመስጠት ከስሜታዊነት ወጥተን አርቆ በማሰብ በሰከነ ኅሊና የውጬን ጫና መክተን በራሳችን ጉዳይ ራሳችንን ባለቤት አድርገን መወያየት ይገባናል (ታከለ፣፳፻፲፤ ፳፻፲፫) ፡፡

የመጻፊያ ፊደል አመራረጥ ጉዳይ ያስነሣው ማዕበል በአሁኑ ጊዜ ሰከን ያለ ቢመስልም ጥሎት የሔደው አሻራ እንደ ገና በትጋት መመርመር ያለበት ጉዳይ እንዲኾን አድርጎታል፡፡ አሁን ጊዜው በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለን በፊደል አመራረጥ ዙሪያ ገንቢ ጥያቄዎችን በማንሣት እንዴት በዚህ ብቸኛ በኾነው አፍሪካ በቀል ፊደላችን መጠቀም እንዳለብን መመርመር ያለብን ጊዜ ነው፡፡

ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ከላይ በተገለጸው መንፈስ አብረን ተባብረን መፍትሔ መፈለግ ይኖርብናል፡፡ ይኸ ቀርቶ ስለ ቋንቋዎቻችን እኛው ራሳችን እናስብበታለን እንጂ ለሌላው ጣልቃ ገብ እንዲከፋፍለን እንዲያለያየን እድል መስጠት የለብንም፡፡ አንድ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ በ፲፱፻፺፬ (በአ.አ.) ኢትዮጵያን ከጎበኘ በኋላ የገለጸውን ሐሳብ እንደሚከተለየው ዶ/ር ታከለ ጠቅሰውታል፡፡

> የአማርኛ ምሁራን ምኞት በአማርኛ ልዩ ፊደል የኦሮምኛንም ቃላት መጻፍ ይቻላል ብለው ፊደሉ ብሔራዊ ፊደል ይኾናልም ብለው ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ ፊደል የሀገሪቱን ዙሪያ ጺጋ አላብሶትም ነበር፡፡ ግን ኦሮሞዎች ፊደሉን አሽቀንጥረው ጥለው ቋንቋቸውን በላቲን ፊደላት ሊገልጹት ወደዱ፡፡ ለዚህም የሰጡት ምክንያት ፊደል በቋንቋቸው የሚገኙትን ድምፆች ሁሉ በግልጽ ሊወክላቸው ስለማይችል ነው ይላሉ፡፡ ለአማሮች ይህ የኦሮሞዎች የአማሮችን ባህል አሽቀንጥሮ መጣልና ከኦሮሞ አካባቢ በሺዎች የሚቆጠሩ የአማርኛ ፊደል ጽሑፎች እልም ብለው ጠፍተው በላቲን ፊደል በተጻፉ የኦሮምኛ ቃላት በመተካታቸው ክፉኛ በጥሬ የተመቱ ያህል ተሰምቷቸው ቅስማቸው የተሰበረ ይመስላል (፲፱፻፺፬፣ ገጽ ፲)

ዶ/ር ታከለ ሲያብራሩ ይህንን ከላይ የተገለጸውን ርካታ ለኦሮምኛ ተናጋሪዎች የገለጸው አሜሪካዊ ነው፡፡ ቅኝ ገዢ የነበሩ ሀገራት ምሁራንም ኾኑ ፖለቲከኞች፡ አፍሪካውያንን በባርነት ቀጥቅጠው ሲገዙ የነበሩ ተናጋሪውን ጨምሮ ለእኛ ለአፍሪካውያን፡ በተለይ ለኢትዮጵያውያን፡ በጎ ነገርን ይመኛሉ ብሎ ማሰብና የነእርሱን ከፋፍሎ የማዳከም ሐሳብ መቀበል አይገባም ይላሉ፡፡ ያዘኑ በመምሰል በመሀላችን ገብተው ሊለያዩን በሚሞክሩበት ጊዜ ሐሳባቸውን መቀበልና የራስን አቃሎ የራስን ጥሎ ከነርሱ ሐሳብ ጋር መወገን የዋህነትና እነርሱን ራሳቸውንም ለትዝብትና ለንቀት የሚዳርግ ይመስላል የሚል አስተያየት አላቸው፡፡

ዋናው ችግር የላቲን ፊደል ባለቤት ነን ባዮች ምዕራባውያኑ ከእኛ ይልቅ ለእኛ የሚጠቅመንን የሚመርጡልን ሊጠቅሙን ሳይኾን እኛን በሐሳብ ለመከፋፈልና የእነርሱን ቅርስ ጠብቀን የእኛን ቅርስና ማንነት አሽቀንጥረን እንድንጥል የሚጋብዙን እንዳይኾን መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ከዚሁም ጋር ያለምክንያት የእኛ ስላልኾነ ብቻ ሌላውንም መጥላት አይገባም፡፡

አሁን እየኾነ ያለውን ኹኔታ ስንዳስስ ግን ሁሉም ብሔር ብሔረሰብ ፊደልን ትቶ ወደ ላቲን ፊደል ከኮበለለ የኢትዮጵያ ፊደል ወደ ሞት እያዘገመ መሄዱ አይቀሬ እንደሚኾን መገመት ከባድ አይኾንም፡፡ የአውሮፓ ሀገሮች የጥንቱን ላቲን ለማቆየት በእርሱም ለመጠቀም ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ስናይ እኛስ ለጥንቱ ኢትዮጵያዊ ቋንቋና ኢትዮጵያዊ የግእዝ ፊደል ምን እናስባለን የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡ የእኛ ለኾነው ነገር ምን ያህል ክብር አለን? ወይስ ሁሌ የራሳችንን ምክንያት ፈጥረን አሽቀጥረን እየጣልን የሌላውን ስንሻ እና ስንፈልግ ለምን እንኖራለን፡፡ 'ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ ባለ እዳ አይቀበለውም' እንዲሉ የእኛ ለኾነ ነገር ትኩረትና ክብር ይኑረን ታሪካችን የማንነታችን መገለጫ ነውና፡፡

አንድ ምሳሌ ብንወስድ የአውሮፓ ጥንታዊ ዩንቨርስቲዎች ማለትም እንደ ኔዘርላንድ ሌይደን ዩንቨርስቲ ዓይነቶች ላቲኑን በቅርስነት ለመጠበቅ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ እንኳ ሲሰጡ በላቲን ፊደልና ቋንቋ አዘጋጅተው ነው፡፡ ያውም በጥንታዊው (old) ላቲን በሚባለው ፊደል፡፡ የራሴን ዲግሪ ለአብነት ማንሣት ይቻላል፡፡ በወቅቱ በሰፊው የሚጠቀሙበት የኔዘርላንድ ቋንቋ ደች እያለ፣ ዓለም የሚጠቀምበት እንግሊዝኛ ቋንቋ እያለ፣ ወይም ሞደርን ላቲንን መጠቀም ሲችሉ ጥንታዊውን ላቲንን መጠቀምን ምን አመጣው ብንል የማንነት ጉዳይ የራስን ሀብት የመንከባከብ፣ የመጠበቅ፣ የማስተዋወቅ ለራስ ቅርስ ሀብትና ማንነት ቦታ የመስጠት ጉዳይ ይመስላል፡፡

ስለዚህ የዓባይን የሕዳሴ ግድብ በራሳችን ሀብትና ጉልበት ገንብተን ሀገራችንን ለማሳደግ የተያያዝነውን የልማት አቅጣጫ የሀገራችንን የብሔር ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎችንም በሀገራችን የግእዝ ፊደል ወደ ጽሑፍ በማሳደግ የራስን ሀብት በራስ በማሳደግ መርሕ ልማታችንን እናፋጥን የሚለው ሐሳብ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ ከሴሜቲክ ውጭ ያሉ ቋንቋዎች የኢትዮጵያን ፊደል ለመጠቀም ምንም ችግር እንደሌለ በተግባር ያሳዩ ቋንቋዎች መኖራቸው በጣም ተስፋ ሰጭ ቢኾንም የኢትዮጵያ ፊደል ከሴሜቲክ ቋንቋዎች ውጭ ለማንም አይኾንም የሚለውን የምዕራባውያኑን ፕሮፖጋንዳ ግን ብዙ ቋንቋዎች ፊደልን ትተው ወደ ላቲኑ አልፋ ቤት ሄደዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ለምዕራባውያን ፌሽታ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ቀጥሎ ያለውን ሰንጠረዥ እንመልከት፣

*ሰንጠረዥ -፱: የላቲን ፊደልን ለጽሑፍ የሚጠቀሙ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች*

| ተ.ቁ | የሴም | የዓባይ ሳህራዊ | የኦሞ | የኩሽ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | - | አኙዋክ | ሸናሻ | ኦሮሚኛ |
| ፪ | - | ኑዌር | ሸኮ | ሲዳሚኛ |
| ፫ | - | መጀንግ | ቤንች | ሀዲያኛ |
| ፬ | - | አፖ | ካፋ | ጌዶ |
| ፭ | - | ኮሞ | ዲዚ | አፋር |
| ፮ | - | በርታ | ኮንታ | ሲዳማ |
| ፯ | - | ጉሙዝ | ወላይታ | ሱማሌ |
| ፰ | - | መኧን | ኮረቴ | ማረቆ |

በተጨማሪም ከኦሞቲክ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ዳውሮ፣ የምና ሸኪቾ በላቲን ጽሑፋቸውን ያሳደጉ ናቸው። በቅርቡ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ሰንጠረዥ -፲: የአፍ መፍቻ ትምህርት የሚሰጥባቸው ቋንቋዎች (ትምህርት ሚኒስትር ፳፻፱)**የአፍ መፍቻ ትምህርት የሚሰጥባቸው ቋንቋዎች (፲፪ ኢት= ፵ ላቲን)

ከዚህ በታች የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጠው ትምህርት እስከ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ እንደ ደረሰ ነው።

| ተ. ቁ | ክልል | በየክልሉ ት/ት/የ ቋ/ ብዛት | ቋንቋዉ ስክሪፕት | በ፳፻፰ በየቋንቋዎቹ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ብዛት | | | ትምህርት የሚሰጥባቸው የቋንቋ ዓይነቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| ፩ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ ክ/መ | ፴፫ | ፬ኢት ፣ ፳፱ ላቲን | ፪፻፵፪፻፻፳፬፻፲ | ፪፻፲፩፻፻፺፻፶፩ | ፬፻፶፬፻፻፶፬፻፳፩ | ዳሽቴ፣ ወላይታቶ፣ ጌዴኦ፣ ሃዲይሳ፣ ካፊኖኖ፣ ስልጢኛ፣ ጋሞኛ፣ ጎፊኛ፣ አይዲኛ፣ ዘይስኛ፣ ጊዲቾ፣ ዳውሮታ፣ ከምባቲሳ፣ ጠምባሮኛ፣ ኮንትኛ፣ ድራይ ታታ፣ ሲዳሙ አፎ ፣ ሀላቢሳ፣ አሪፋ፣ ባስኬቶኛ፣ ሱርማ፣ ዲዚኛ፣ ቤንቺኛ፣ ሽኮኛ፣ መኤኒትኛ፣ የምሳ፣ መዠንገር፣ ሽኮ፣ ኮሬቴ፣ ሽኪኖኖ፣ ማረቆኛ/ሊቢዲኛ፣ ቀቤንኛ፣ ማሌኛ |
| ፪ | ትግራይ | ፫ | ፫ ኢት | ፳፯፻፻፴፱፻፳፬ | ፳፫፻፻፹፭፻፸፱ | ፻፴፻፻፳፭፻፵፫ | ትግርኛ ፣ ሳሆ፣ ኩናማ |
| ፫ | ሐረሪ | ፫ | ፪ ኢት፣ ፩ ላቲን | ፬፻፻፵፬፻፳፩ | ፫፻፻፺፩፻፮ | ፳፻፻፴፭፻፳፳ | አማርኛ፣ ሐረሪ፣ አፋን ኦሮሞ |
| ፬ | አፋር | ፫ | ፪ ኢት ፣ ፩ ላቲን | ፳፻፻፳፪፻፹፯ | ፲፳፻፻፺፮፻፹፪ | ፴፱፻፻፳፻፳፳ | አፋርኛ፣ አማርኛ፣ አርጎብኛ |
| ፭ | ሶማሌ | ፩ | ፩ ላቲን | ፶፳፻፻፯፻፲፱ | ፴፮፻፻፲፱፻፸፪ | ፺፭፻፻፳፭፻፺፩ | አፍ ሶማሌ |
| ፯ | የጋምቤላ ሕዝቦች | ፭ | ፭ ላቲን | ፬፻፻፸፫፻፸፯ | ፭፻፻፪፻፹ | ፱፻፻፸፯፻፳፱ | ኮሞኛ፣ አኙዋክኛ፣ መጃንግኛ ኦፖኛ፣ ኑዌርኛ |
| ፮ | አዲስ አበባ ከ/ አስ | ፩ | ፩ ኢት | - | - | ፳፳፻፻፶፱፻፴፩ | አማርኛ |
| ፳ | ኦሮሚያ | ፪ | ፩ ኢት፤ ፩ላቲን | ፬፻፻፺፻፴፮ | ፬፻፳፪፻፻፹፻፵፫ | ፱፻፲፫፻፻፲፮፻፶፱ | አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ |
| ፱ | አማራ | ፬ | ፫ ኢት፣ ፩ ላቲን | ፪፻፳፫፻፻፲፪፻፹፬ | ፪፻፲፯፻፻፭፻፹፩ | ፬፻፴፱፻፻፲፳፻፳፭ | ህምጣኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ አዊኛ፣ አማርኛ |
| ፲ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | ፫ | ፫ ላቲን | - | - | ፲፻፻፳፬፻፶፯ | ጉሙዝኛ፣ በርታኛ፣ ሽናሽኛ |
| ፲፩ | ድሬዳዋ ከ/ አስተዳደር | ፫ | ፪ ላቲን፤ ፩ ኢት | ፬፻፻፲፳፻፴ | ፫፻፻፸፻፳ | ፮፻፻፹፳፻፶ | አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሶማልኛ |
| | ጠቅላላ ድምር | ፳ | ፲፯ ኢት፣ ፵፬ ላቲን | ፲፩፻፲፬፻፻፲፱፻፯ | ፱፻፹፫፻፻፵፬፻፳፳ | ፳፩፻፴፯፻፻፵፮፻፳፩ | አጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥባቸው ቋንቋዎች፡ ፶፪ናቸው |

## ሰንጠረዥ -፲፩፡ በከፍተኛ ተቋማት እስከ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ የዋሉ ቋንቋዎች

| ተ.ቁ | የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ዓይነት | የሚጠቀሙት ስክሪፕት | አገልግሎት የሚሰጡበት ክልል | ቋንቋዎች አገልግሎት የሚሰጡባቸው ተቋማት | | | | | የአገልግሎት ዓይነት | | | አገልግሎት መስጠት የጀመሩበት ጊዜ | የአገልግሎት ዘመን ብዛት | በጥናቱ ወቅት በየቋንቋዎቹ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከ፩-፬ኛ | ከ፭- | ከ፱-12ኛ | በመ/ት/ | በዩ/ሲ | በት/ት ዓይነትነት | በት/ት መስጫነት | በሁለቱም | | | |
| ፩ | ሲዳሙ አፎ | ላቲን | ደቡብ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | “ | “ | “ | ፲፱፻፺፫ | ፳፫ | ፱፵፻፱፸፫፱ |
| ፪ | ወላይታት | ላቲን | ደቡብ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | “ | “ | “ | ፲፱፻፺፫ | ፳፫ | ፴፩፻፱፴፮፻፲፰ |
| ፫ | ሃዲይሳ | ላቲን | ደቡብ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | “ | “ | “ | ፲፱፻፺፭ | ፳፪ | ፴፰፻፱፸፯፻፴፭ |
| ፬ | ጋሞኛ | ላቲን | ደቡብ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | “ | “ | “ | ፲፱፻፺፫ | ፳፫ | ፵፩፻፱፸፫፻፯ |
| ፭ | ትግርኛ | ሳባ | ትግራይ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | በት/ት ዓይነትነት | በት/ት መስጫነት | በሁለቱም | ፲፱፻፹፫ | ፴ | ፻፳፱፻፱፴፰፻፭፰ |
| ፮ | አፍ ሶማሌ | ላቲን | ሶማሌ፣ ድሬዳዋ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | በት/ት ዓይነትነት | በት/ት መስጫነት | በሁለቱም | ፲፱፻፺፭ | ፳፪ | ፶፫፻፱፶፪፻፳፫ |
| ፯ | አማርኛ | ሳባ | አማራ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ | ከ፩-፬ኛ | ከ፭-፰ኛ | ከ፱-፲፪ኛ | መ/ት/ቤ | ዩ/ሲ.ቲ | “ | “ | “ | ፲፱፻፺፭ | ፳ | ፯፻፶፫፻፱፫፻፲፩ |

(ትምህርት ሚኒስትር ፳፻፱)

እነዚህ ቋንቋዎች ወደ ጽሑፍ ሲያድጉ ከኢትዮጵያ ፊደል ይልቅ ወደ ላቲን የወሰዳቸው ጉዳይ ምንድነው ስንል ዋና ዋና የኾኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው አንዱ የኢትዮጵያ ፊደል ከሴሜቲክ ውጪ ለኾኑ ቋንቋዎች ፊደል ኾኖ ሊያገለግል አይችልም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም በኢትዮጵያ ፊደል አጠቃቀም ላይ የላቲኑንና የኢትዮጵያን ፊደል የተጠቀሙትን ስናይ ከሴሜቲክ ቋንቋዎች ታናጋሪ ውስጥ ላቲንን የተጠቀመ አንድም የለም፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ከሴሜቲክ ውጭ ያሉት ቋንቋዎች በአብዛኛው የተጠቀሙት ላቲንን ነው፡፡ ወደ ላቲን የወሰዳቸውም የኢትዮጵያ ፊደል የአናባቢንና ተናባቢን ርዝመት ለመለየት አይችልም ስለዚህ ወደ ላቲን መሄድ አለብን፣ የሚለው አደናጋሪ ሐሳብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፖለቲካ በማኅበራዊ ግንኙነት ከኢትዮጵያ ፊደል ይልቅ ላቲኑ ይሻለናል የሚል አዝማሚያም ከፖለቲከኞቹም የተጨመረ አለ፡፡

ከዚህ ለበለጠ መረጃ ዶ/ር ጥላሁን ገምታ (፲፱፻፹፬) በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሠጡት ሐሳብ ከኢትዮጵያ ፊደል ይልቅ ላቲን ለመጠቀም በምክንያትነት የነበሩ ጉዳዮችና እንደ ችግር የተጠቀሱ ሁሉ በአሁኑ ወቅት የተቃለሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ ከኢትዮጵያ ፊደል ይልቅ ለኮምፒዩተር ጽሑፍና ለዓለም አቀፍ ምርምር ላቲኑ ይሻላል በሚሉት በዶ/ር አበራ (፲፱፻፺፩) ሞላ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎችም ላይ እንደ ተመለከተው የኢትዮጵያን ፊደል ያለምንም ችግር በኮምፒዩተር ለመጠቀም ቴክኖሎጂው እየፈታው መጥቷል፡፡ ሌላው እንደ ምክንያት የቀረበው ልጆቻችን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በላቲን ከተማሩ እንግሊዝኛና ፈረንሳይን ለመማር ይቀላቸዋል፣ የሚለው አባባል ሲኾን ለኦሮምኛ ተናጋሪዎች ኦሮምኛን ለመማር የላቲንን ፊደል መጠቀማቸው እንግሊዝኛን ለመማርም ኾነ ለማንበብ አደናገራቸው እንጂ ሲጠቅማቸው አላየንም፡፡

ስቴቨን እንዳስቀመጠው የአፍሪካ ሀገር በቀል በኾነው የባንቱ ቋንቋ እንኳ አውሮፓያውኑ ርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ትንቅንቅ ዳፋ ውስጥ ወድቆ ሦስት ዓይነት የጽሑፍ ሥርዓት እንደ ተፈጠረለት ይጠቅሳል፡፡ እነርሱም የእንግሊዝ፣ የጀርመንና የፈረንሳይን ድምፆች የሚወክሉ አጻጻፎች ተፈጥረውለት እንደ ነበር ያትታል (ስቴቨን፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፯)፡፡

## ፩. የኢትዮጵያን ፊደል ለሁሉም ቋንቋዎች መጠቀም መቻሉ

ቀደም ሲል በመጠኑ የተመለከትነውን ማለትም ሁሉም የሀገሪቱ ቋንቋዎች የግእዙን ፊደል መሠረት አድርገው የየራሳቸው ንጥረ ድምፅ ላይ መሠረት ያደረገ የየራሳቸው የፊደል ገበታ መሥርተው ወደ ጽሑፍ ማደግ ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ ሰፋ አድርገን ከሥነ-ልሳን መርሕ፣ ከማንነት ከታሪክና ከቅርስ አኳያ እንደሚከተለው እንዳስሰዋለን፡፡

## ፳.፩. ከሥነ-ልሳን መርሕ

የኢትዮጵያ ፊደል የምንለው መጀመሪያ ለግእዙ በኋላም ለአማርኛው ሲያገለግል የነበረው፣ ሀገሪቱ ከጥንት ጀምሮ በራሷ የጽሑፍ ሕግና ሥርዐት ስትጠቀምበት የኖረችውን ፊደል ነው። በታሪክ አጋጣሚ ግእዙ ከሳቢያን ወይም ሳቢያኑ ከግእዙ የተዋዋሷቸው ነገሮች ቢኖሩ ይህ ተፈጥሯዊ ነው፤ ነገር ግን የተፈጠረው ፊደል የኢትዮጵያ ፊደል ነው። አማርኛና ሌሎች ብዙ የሀገሪቱ ቋንቋዎች የኢትዮጵያን ፊደል በመጠቀም የራሳቸውን የጽሑፍ ሥርዐት ፈጥረዋል። ይህ ኢትዮጵያዊ ፊደል ደግሞ ለሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሁሉ እንደየ ቋንቋዎቹ የድምፅ ባሕርይ ተዘጋጅቶና በልጽጎ ሊያገለግል እንደሚችል የሥነ-ልሳን ሙያ ያረጋግጣል[1]። ለዚህ ያሉት ጅማሬዎችም ምስክሮች ናቸው። ወደ ፲፪ የሚደርሱ ሀገር በቀል ቋንቋዎች የኢትዮጵያን ፊደል ተጠቅመው ወደ ጽሑፍ ማደጋቸው ሌሎችም ፊደልን ለመጠቀም የሚያግዳቸው ነገር የሌለ መኾኑን ያሳያል። የሀገር በቀል ቋንቋዎቻችን የሥነ ድምፅ ባሕርይ በአብዛኛው ተመሳሳይነት አለው። ለምሳሌ፦ ተስፈንጣሪ ድምፆች የሚባሉት ቀ፣ ጠ፣ ጨ፣ ጰ፣ ጸ ወዘተ በብዙ የሀገር በቀል ቋንቋዎች ውስጥ ይገኛሉ (ባየ፣ ፲፱፻፹፩)። የኩሻውያን የሴማውያን የኦሞያውያንም ኾነ የናይሎ ሰሃራ ቋንቋዎች የነዚህ ድምፆች ባለቤቶች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ድምፆች በላቲኑ ፊደል ውስጥ የሉም። የኢትዮጵያን ፊደል መጠቀሙ እነዚህን ንጥረ ድምፆች በየቋንቋዎቹ ያለ ችግር ፊደል በመወከል ወደ ጽሑፍ ማሳደግ ይቀላል።

የኢትዮጵያ የኾነውን የግእዝ ፊደል እንጠቀም ሲባል ግእዝን ከነጓዙ እንጠቀማለን ማለት ሳይኾን ፊደል ከሚቀረጽለት ቋንቋ የድምፅ ባሕርይ አንጻር የሚወሰን ይኾናል (ሙሉጌታ፣ ፳፻፲፮፤ ፳፻፳)።

ለምሳሌ የኦሮምኛ ቋንቋ የኢትዮጵያን ፊደል ቢጠቀም /dh/ የሚለውን ንጽረ ድምፅ ለመወከል ሌሎቹ የኢትዮጵያን ፊደል የሚጠቀሙ ቋንቋዎች የሚጠቀሙበትን /ዽ/ የሚል አዲስ ንጽረ ድምፅ ከመፍጠር ውጪ ሌሎቹ ድምፆች ያለምንም ተጨማሪ ፈጠራ በኢትዮጵያ ፊደል ሊወከሉ ይችላሉ። ይሄ ቀደም ሲልም መሠረተ ትምህርት በኦሮምኛ ሲሰጥና መጽሐፍ ቅዱስ በኦሮምኛ ሲጻፍ ወይም ሲተረጐም ያለምንም ችግር በኢትዮጵያ ፊደል ነበር የተጻፈው። ኾኖም ምዕራባውያኑ በዘረጉት አሠራር ነው ላቲንን መጠቀም አማራጭ የሌለው መስሎ በማቅረብ ፊደልን ከጨዋታ ውጭ ያደረጉት። ለምሳሌ በኦሮምኛው የላቲን ፊደል ላይ ልዩነት ላላቸው ድምፆች አዳዲስ

[1] ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች የፊደል ገበታ ላቲን ወይስ የኢትዮጵያ ፊደል በሚል ርእስ በትግራይ ክልል ሐውዜን ላይ ፳፻፱ በተከበረ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በዓል ላይ በባሕር ዳር ለሚዘጋጅ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ያዘጋጀሁትን የጥናት ወረቀት አቅርቤ ብዙ መነቃቃት ስለ ፈጠረ ጥናቱ በዚያኑ ዓመት ባሕር ዳር ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ እንዳይቀርብ ነው የታገደው። ላቲን በኢትዮጵያ ፊደል ላይ የሚያደርገውን የጥፋት ዘመቻ ይገታዋል ተብሎ ስለ ተሠጋ። በወቅቱ የነበረው የፊደል ተጽእኖ መዋቅራዊ ድጋፍ እንደ ነበረው ያሳያል።

ድምፆች ለመወከል ሁለት ምልክቶችን በመጠቀም ከዐምስት በላይ ድምፆችን መፍጠር ይጠይቃል። በኢትዮጵያ ፊደል ቢኾን ግን ምንም ዓይነት ተጨማሪ ሥራ ሳያስፈልግ መጠቀም እንደሚቻል ያሳያል።

ርዝመትና ጥብቀት እንደ ላቲኑ ሁሉ ድምፅን በመደጋገም ወይም የሚያሳዩ ምልክቶችን በመጠቀም የጽሑፍ ሥርዐቱን ማስኬድ ይቻላል። ብዙ ግዜ ግን ምክንያት ሊኾኑ የማይችሉ ጉዳዮችን በመምዘዝ ፊደልን ማጥላላት ተገቢ አይደለም። ለአብነት ያህል የአፋን ኦሮሞ ንጽረ ድምፅን መሠረት ያደረጉ የላቲን ፊደላትን ቀጥሎ እንመልከት (ደሳለኝ፣ ፳፻፳፩፣ ገጽ ፻፴)።

The recommended orthography of Oromo

Upper case A B C’ Ch D Dh E F G H I J K K’ L M N

Lower case a b c’ ch d dh e f g h i j k k’ l m n

Letter name [a] [ba] [c’a] [tʃ’a] [da] [ɗa] [e] [fa] [ga] [ha] [i] [dʒa] [ka] [k’a] [la] [ma] [na]

Upper case Ny O P P’ R S Sh T T’ U V W Y Z Zh ʔ

Lower case ny o p p’ r s sh t t’ u v w y z zh ʔ

Letter name [ɲa] [o] [pa] [p’a] [ra] [sa] [ʃa ] [ta] [t’a] [u] [va] [wa] [ja] [za] [ʒa] [ʔa]

### የኢትዮጵያ ፊደል ለኦሮምኛ ቋንቋ

**ልዩ የኾኑት፤** /ጭ-C/፣ ጵ-ph/፣/ድ-dh/፣/ቅ-k’/፣/ኝ-ng/፣/ጥ-t’/፣/ሽ-sh/

**የተለየያልኾኑ**
/ት-t/፣/ክ-k/፣ /ብ-b/፣/ድ-d/፣ /ግ-g/፣ /ፍ-f/፣/ስ-s/፣/ዝ-z/፣/ህ-h/፣/ፅ-ts’/፣/ን-n/፣ /ም-m/፣/ል-l/፣ /ር-r/፣ /ይ-j/፣/ው-w/

ከዚህ በላይ ከተገለጸው ምሳሌ እንደምንረዳው የኦሮምኛን ፊደል ንጥረ ድምፅ በኢትዮጵያ ፊደል ብንወክል ምናልባትም ከአንድ ፊደል ከ /ድ/ በስተቀር ያለምንም ማስተካከል ሁሉም ድምፆች በኢትዮጵያ ፊደል መተካት ይችላሉ። በላቲኑ ግን ከላይ እንዳየነው ብዙ አዳዲስ ምልክቶች መፍጠር ያስፈልጋል። የጽሑፍ ዘዴ ብዙ ነገሮችን አካቶ ይይዛል። አቶ ገላውዲዎስ አየለ በከሪን ንግግር ጠቅሰው ሲናገሩ፦

የጽሑፍ ዘዴ የዕውቀት ዘዴ አንዱ አካል ነው፤ ጽሑፍ ሲተረጐም ፍልስፍና ነው፤ ምክንያቱም ሐሳብን፤ አመለካከትን፤ ተግባራትን፣ ምልክትን፣የምስልን እና ሌላ ሥዕላዊ ነገሮች መግለጽ ነው። በተለይ የጽሑፍ ሥርዐት ሕዝብ እንቅስቃሴዎቹን እና ሐሳቡን በምልክት የሚያስቀምጥበት ዘዴ ነው። ጽሑፍ ሐሳብ በንጥረ ድምፅ ተቀናብሮ የሚገለጽበት ነው። ከዚህም በበለጠ ታሪካዊ ማንነትን የሚያሳይ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገርበት ነው (ገላውዲዎስ፣ ፳፻፬)።

*ሰንጠረዥ -፲፪፡ የኢትዮጵያ ፊደል*

| | Ge'ez a | Ka'eb u | Salis ī | Rab'e a | Hamis é | Sadis i | Sab'e o |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| h | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| l | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ḥ | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| m | መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| s | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| r | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| s | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| q | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| b | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| t | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| h | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| n | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| a | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| k | ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| w | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ạ | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| z | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| y | የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| d | ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| g | ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ṭ | ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| p̣ | ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ts | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ts | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| f | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| p | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

አንድን ፊደል ለጽሑፍ ስንጠቀም ከሥነ ልሳን መርሑም ባሻገር የተለያዩ ምሁራንን ማሳተፍ ለምሳሌ የኅብረተሰብ ሳይንስ፣ የሥነ ልቡና፣ የፖለቲካል ሳይንስ፣ የኢኮኖሚክስ ሳይንስና የአንትሮፖሎጂ ሳይንስ ባለሙያዎችን ማሳተፍ እንደሚገባ ምሁራን ይገልጻሉ (ፊሽማን ፲፱፻፹፰፣ ገጽ ፪፻፹፬)።

የንጥረ ድምፅ ጥብቀትና ርዝማኔን በተመለከተ በሥርዐተ ጽሑፉ ለማሳየት በፊደልም መፍትሔ አለው። ፊደልን በመጠቀም የተናባቢ ጥብቀትን ማሳየት ይቻላል። ለምሳሌ በማሌ ቋንቋ ላይ የተናባቢን ጥብቀት፣ የአናባቢን ርዝመት እንደ ላቲኑ ሁሉ ፊደልን በመድገም ድምፁን ማሳየት ይቻላል። ምሳሌ፦

| | | |
|---|---|---|
| ቢስሲ | bissi | ‘placenta’ |
| ሶኦፐፔ | sooppe | ‘fontanel’ |

ፊደልን መጠቀም ከሥነ ልሳን መርሕ አንጻር ብዙ አሳማኝ ነጥቦች ማንሣት ይቻላል፡ ፡ የሀገር በቀል ቋንቋዎችን በቀላሉ ለመማር አንዱ ተናጋሪ የሌላውን ፊደልና ቋንቋ ለማጥናት አንድ ዓይነት ሀገራዊ ፊደል ቢጠቀሙ ይቀላል። ፊደል አጻጻፉና አነባበቡ አንድ ዓይነት ስለ ኾነ ለመማርም ኾነ ለማስተማር ቀላል ነው። በሌላ በኩል ፊደል ተናባቢና አናባቢ በአንድ ምልክት የሚያሳይ ስለ ኾነ ብዙ ቦታ ስለማይፈጅ ለቦታ ቁጠባ ይጠቅማል (ታከለ፣ ፳፻፲፤ ፳፻፲፫)። ከዚህም በተጨማሪ ሀገር በቀል ዕውቀትንና የሀገር ቅርስን ያሳድጋል። ስለዚህ ፊደልን ጥለን ወደ ላቲን የምንሄድበት ምንም ዓይነት በሥነ ልሳን ሳይንስ የተደገፈ አሳማኝ ነገር የለም የፖለቲካ ውሳኔ ካልኾነ በቀር።

### ፭.፪. ከማንነት ማሳያ አንጻር

ግሬኖብል (፳፻፯፣ ገጽ ፻፵፬) ኮውልማስን (፲፱፻፹፱) ጠቅሶ እንደሚለው የፊደል መረጣ ብዙዎች የራሳቸውን ፊደል በተለይም ከላቲኑ ይልቅ ፊደልን ለመምረጥ የሚያነሣሣቸው ፊደል የማንነት ማሳያ በመኾኑ ነው። እስራኤልን ብንወስድ ሒብሪውን ከሞተበት ፈልጋና ሕያው አድርጋ በራሷ ፊደል መጻፏ ጥንታዊ የእስራኤልን ማንነትና ታሪክ ሊያንጸባርቅ እንደሚችል በማሰብ እንደ ኾነ ጸሐፍት ይናገራሉ።

እንደዚህ ዓይነቱ የራስን ቋንቋ በራስ ፊደል የመጠቀም ፍላጎት በአፍሪካውያን ዘንድ ከተነሣሣ የቆየ ነው። ኾኖም ግን በቅኝ ገዢዎች ተጽእዕኖ ሲማቅቅ ኖሮ አሁንም ነጻነት ተነፍጎት ያልተፈታ እንቆቅልሽ ኾኖ ቀርቷል።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ፊደል የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የምርምር እና የፍልስፍና ሀብት ነው። ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል፣ የራሷ ቍጥር፣ የራሷ ዘመን አቈጣጠር ወዘተ የሚለው ሁሉ የኢትዮጵያ ሊቃውንትን ጥበብና የፍልስፍናን ርቀትና ጥልቀት የሚያሳይ ነው። ችግር የኾነው ግን ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ...ኾነና ነው። በዚህ ጥናት የተጠቀምነው ንድፈ

ሐሳብ ስፐሯት (፳፻፪) የፈጠረው ኮምፒዩቴሽናል የጽሑፍ ዘዴ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ጥናቱ ተንታኝ የገለጻ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡

የጥናቱ መረጃዎች ተመራማሪው ለፊደል ቀረጻ ወደ ማሌ ወረዳ፤ ሣላማጎ ወረዳና በደቡብ ክልሎች ከተሠማራባቸው አካባቢዎች የተለያዩ ቋንቋ ተናሪዎች መረጃ ሰጪዎች የተሰባሰቡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ መጽሐፎችና የጽሑፍ መረጃዎች፣ ከተመራማሪው የዕለት ከዕለት ምልከታዎችና የመረጃ መረብ ወዘተ ለማሰባሰብ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ጥናት የኢትዮጵያ ፊደል ለሀገር በቀል ቋንቋዎች ሁሉ የፊደል ገበታ መኾን ይችላል አይችልም? ከላቲኑና ከኢትዮጵያ ፊደል ለሀገር በቀል ቋንቋዎች በፊደልነት ለመጠቀም የቱ ምክንያታዊ ነው? በዚህ ዙሪያ ያሉ ትርክቶች ምንጫቸው ምንድን ነው? የሚለውን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ሀገር በቀል ቋንቋዎቻችን ፊደልን በመጠቀም ወደ ጽሑፍ ቢያድጉ የሚኖረውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ለማሳየትም ተሞክሯል፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የራሱን ፊደል ቢጠቀም ከሀገር አንድነትና ማንነት ጋር ያለውን ትስስር የበለጠ ያጠነክረዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ዓይነት ፊደል መጠቀሙ ለአጻጻፍ ሥርዐትም ለትምህርት ቁሳቁስ ዝግጅትም በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ ለሚደረጉ የሥራ ክንውኖች ውጤታማነት አጋዥነት ይኖረዋል፡፡

የማንም ቋንቋ ፊደል የተወሰነ መሻሻል እስካልተደረገለት ድረስ ሙሉ ለሙሉ የሌላውን ቋንቋ ፊደል ሊወክል ወይም ሊያሟላ አይችልም፡፡ ይኹንና ለአንድ ቋንቋ ፊደል ስንቀርጽ የቋንቋውን ሥነ ድምፅ በደንብ ለይተን በቋንቋው ሥነ ድምፅ ልክ ፊደል መቅረጽ ይጠበቅብናል፡፡ ሰው ልብስ መልበስ ያለበት ለብሶም ማማር የሚችለው ተለክቶ በልኩ አሰፍቶ ወይም ገዝቶ ሲለብስ ነው፡፡ ለቋንቋም ፊደል መቅረጽ እንዲሁ ነው፡ ፡ ግእዝ ፊደል የተቀረጸለት በልኩ ስለ ኾነ አጠቃቀሙ ያማረ የተዋበ ነው፡፡ አንድም ፊደል መቀነስ አይቻልም፤ ሁሉም ጥቅም ሁሉም ሥራ አላቸው፡፡

አማርኛ ግን ፊደል ሲቀረጽለት በልኩ ሳይኾን በግእዝ ልክ ስለ ኾነ ፊደሉ ሲያከራክር ኖሯል፡፡ ለምሳሌ በግእዙ ሠ እና ሰ የተለያዩ ንጽረ ድምፆች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንዱንም መቀነስ አይቻልም፡፡ በቃላት ውስጥ የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ፡፡ ለምሳሌ፦ ሠረቀ ማለት ወጣ ነው፡፡ ሰረቀ ማለት ደግሞ ሰረቀ ነው፡፡ በአማርኛው የነዚህ ንጥረ ደምፆች መለያየት የተለየ ትርጉም አያመጣም፡፡ ምክንያቱም ለአማርኛ ወጣና ሰረቀ የተለያዩ ንጽረ ድምፅ የሚጠቀሙ ቃላት ናቸው፡፡ ስለዚህ ሠረቀ/ሰረቀ የሚለውን ቃል አማርኛ ተናጋሪ አንድ ቃል አድርጎ ስለሚመለከተው አንዱ ንጥረ ድምፅ ቢቀነስና አንዱን ብቻ መጠቀም ቢቻል የሚፈጥረው ችግር የለም፡፡ የግእዝ ተናጋሪ ግን ለእርሱ የተለያዩ ቃላት ናቸው፡፡ ይኹንና በአማርኛ የተጻፉ በዘመናት የፈሩ ብዙ ዶክመንቶች ስላሉ ፊደሉን

መነካካት አያስፈልግም የሚባለው የነበሩት ፊደላት ከተቀነሱ ትውልዱ ምናልባት የቀደሙ ጽሑፎችን አንብቦ ለመረዳት እንዳይቸገር መጠንቀቅ ያስፈልጋል በሚል ነው፡፡

ማንም ፊደል በራሱ ምሉእ ነው ማለት ያስቸግራል፡፡ የአንድን ቋንቋ ፊደል ለሌላው ቋንቋ ፊደል አድርጎ ለመጠቀም የተወሰኑ ንጥረ ድምፆች ላይ ማስተካካያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የላቲኑን ፊደል ጉድለት ለማሟላት በየቋንቋው አዲስ ድምፅ ለመወከል በብዙ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ የሚደረገውን ሙከራ መመልከቱ በቂ ይኾናል፡፡ ከዚህም ባሻገር በሀገራችን የላቲኑ ፊደል አጠቃቀም ባሳደረው ተጽእኖ ምክንያት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያስከተለው ችግር ቀላል አይደለም፡፡ በላቲኑ ሲማሩ የቆዩ ብዙ ተማሪዎች ወደ እንግሊዝኛው ሲመጡ በተመሳሳይ ድምፆች አነባበብ ሂደት ላይ ብዙ  ሲቸገሩ ይታያል፡፡

ስለዚህ የፊደላችንን ጉድለት እያሟላን፣ ለሁሉም ቋንቋዎች አገልግሎት በሚሰጥበት ኹኔታ የሥነ ልሳን ሙያ በሚያስገነዝበን መሠረታዊ ዕውቀት መሠረት እየቃኘን መጠቀሙ የሚበጅ ይመስላል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሁሉ በኢትዮጵያዊው ፊደል በግእዝ የፊደል ገበታነት ቢጠቀሙ አንድ ሰው ከራሱ ቋንቋ ሌላ ቋንቋ መማር ቢፈልግ የሚያጠናው ከራሱ ውጭ ያሉትን ጥቂት ፊደላት ብቻ ይኾናል፡፡ ስለዚህ የሀገር በቀል ቋንቋዎችን በመማር በማስተማሩ ሂደት በኩል ጥሩ መፍትሔ ሊኾን ይችላል፡፡ ይህን የኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን የአፍሪካና የዓለም ቅርስና የኢትዮጵያም ኩራት የኾነውን ፊደል ለማቆየት ይረዳል፡፡

የዚህ ዓይነቱ ስሜትና ግፊት በግዴታ ሳይኾን በፈቃድና በግንዛቤ ላይ ከተመረኰዘ የቋንቋ ተናጋሪውንም አስተሳሰብ ወደ መልካም አቅጣጫ ያመላክተዋል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያን ፊደል መጠቀሙ በብዙ መልኩ ጠቃሚ ነው፡፡ ዛሬ በላቲን የተማሩ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች የእንግሊዝኛውን ፊደል C ን ጨ ተብለው ተምረው ኮካኮላ (cocacola) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ጮጫጮላ ብለው በማንበብ ለስሕተት አይዳረጉም ነበር፡፡

ከላቲኑ ይልቅ ፊደልን መጠቀም የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥቅሞች ያስገኛል፡፡

፩) ሀገር በቀል ዕውቀትንና የሀገር ቅርስን ያሳድጋል

፪) የሀገር በቀል ቋንቋዎችን በቀላሉ ለመማር አንዱ ተናጋሪ የሌላውን ፊደልና ቋንቋ ለማጥናት አንድ ዓይነት ሀገራዊ ፊደል ቢጠቀሙ ይቀላል

፫) ፊደል አጻጻፉና አነባበቡ አንድ ዓይነት ስለ ኾነ ለመማር ማስተማር ይቀላል

፬) ፊደል ተናባቢና አናባቢ በአንድ ምልክት የሚያሳይ ስለ ኾነ ብዙ ቦታ ስለማይፈጅ ለቦታ ቁጠባ ይጠቅማል፡፡

ስለዚህ እኛ በጥቃቅን ነገር እየተለያየን ሌሎች የራሳቸውን እንዲጭኑን እድል መስጠት የለብንም፡፡ በዓባይ ግድብ የጀመርነውን የራስን ሥራ በራስ ሀብት የመገንባት ሥራ ወደ ቋንቋዎቻችንም በማምጣት በራሳችን ፊደል ሀገር በቀል ቋንቋዎቻችን የማሳደግ ሥራ ተባብረን መሥራት፣ እንዲሁም በስሜታዊነትና በጊዜያዊ ጥቅም የሀገር ሀብትንና ቅርስን አሳልፎ ከመስጠት መቆጠብ ይጠቅመናል፤ ይጠበቅብናልም፡፡ ካሣዬ (፳፻፩፡ ገጽ ፬) የፊደል ሐውልት በሚለው ጥናታቸው ላይ እንደ ጠቀሱት አንድ ቋንቋ የራሴ በማይለውና የባዕድ በኾነ ምልክት መጠቀም ከጀመረ ቀስ በቀስ ከራሱ የማንነት ዐውድ እየወጣ የማንነቱን አሻራ እያጣ ይሄዳል እንዳሉት የእኛም ዕድል ይህ እዳይኾን መጠንቀቅ ይገባል፡፡

በኅብረተሰቡ ዘንድ የኢትዮጵያ ፊደልን አጠቃቀም በተመለከተ የተነዙ ቅርስና ማንነትን አናግተው ወደ ላቲን የወሰዱ አፍራሽ መረጃዎች በደንብ ሊጠኑ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ የራሷን ፊደል በመጠቀም ከራሷም አልፋ ለአፍሪካም አፍሪካዊ ፊደልን በማጋራት ትልቅ ሚና መጫወት ይጠበቅባታል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከታሪክ፣ ከፖለቲካና ከማንነት ጥያቄ ጋር አያይዘው የጉዳዩ ባለቤቶች ማለትም የቋንቋው ተናጋሪዎች፣ የቋንቋው የጥናት ባለሙያዎች እና መንግሥት በሚገባ ሊያጤኑት ይገባል፡፡ አለበለዚያ ሁሉም ቋንቋዎች ወደ ጽሑፍ ሲያድጉ የኢትዮጵያን ፊደል ከግንዛቤ እጥረት የተነሣ መጠቀም ትተው በየራሳቸው መንገድ ከተጓዙ ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል ያላት ሀገር ናት የሚለው አባባል ታሪክ ኾኖ መቅረቱ የማይቀር አደጋ ነው፡፡

እንደ መፍሔው ሐሳብ ሊቀመጥ የሚችለው በፊደል ቀረጻዎቻችን ዙሪያ እንደ ገና ቁጭ ብለን ልንወያይ ልንመካከር ያለፍንባቸውንም የፊደል ቀረጻ ሂደቶች በራሳችን መንገድና ከሌሎች ተጽእኖ ነጻ በኾነ ኹኔታ እንደ ገና ልንፈትሽ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አፍሪካዊና ዓለም አቀፍ ገጠመኞችንም መቃኘት ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሚመለከተው ተቋምም ኾነ ግለሰብ የሀገር በቀል ዕውቀቶቻችንን በማሳደግና በጋራ በመጠቀም ረገድ የየበኩሉን ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡ በፊደል አጠቃቀም ዙሪያ ሰፊ ጥናቶች ሊከናወኑ ባጋጠሙ ችግሮችም ላይ ሰፊ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥናት ገባኤዎች በማዘጋጀት ምሁራን በጉዳዩ ዙሪያ በሰፊው እንዲወያዩበት መንግሥትም ኾነ የሚመለከተው አካል እድል መፍጠር ይኖርበታል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል። (፳፻)። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ። ብርሐንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ባየ ይማም። (፲፱፻፹፬)። *ሥርዓተ ጽሕፈት ውይይት። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር መጽሔት፣ ፫(፩)፣ ገጽ ፲፯ — ፵፩።*

ታከለ ታደሰ። (፳፻፲፫)። *የኢትዮጵያ ቁልፍ ችግር።* ቲ.ኤም ማተሚያ ቤት።

ታከለ ታደሰ። (፳፻፲)። *የቋንቋ አጠቃቀም በኢትዮጵያ።* ዘካርያስ ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ሚኒስትር (፳፻፱)። *በኢትዮጵያ ትምህርት የሚሰጥባቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መረጃ።* በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ልማት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ(አለቃ)።(፲፱፻፵፰)።*መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ።* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አበራ ሞላ። (፲፱፻፺፩)። የአማርኛ የጥናት ጽሑፎች በኢትዮጵያዊ ፊደል እንዴት ኮምፒተራይዝድ መኾን ይችላሉ። በኢትዮጵያ የሪቪው ማጋዚን (ጥር ፲፱፻፺፩).።

አእምሮ በሪሁን። (፳፻)። *የኢትዮጵያ ፊደል ታሪክ እና ክፍለ ዘመን። አዲስ አበባ ኤስ ኤን ማተሚያ ቤት።*

አስረስ የኔሰው። (፲፱፻፺፩)። *የካም መታሰቢያ የኢትዮጵያ ፊደል መሠረትና መታወቂያ።* አስመራ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት።

ኑኃሚን ዋቅጅራ። (፳፻፪)። *ማኅቶተ ጥበብ ዘልሳነ ግእዝ።* አንደኛ መጽሐፍ. ማኅበረ ቅዱሳን።

ዘርዓ ዳዊት አድሐና። (፲፱፻፺፪)።*መርኆ-ሰዋሰው ዘልሳነ ግእዝ።* ብርሐንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ጥላሁን ገምታ። (፲፱፻፹፬)። ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተሰጠ ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት ፳፬፣ ፲፱፻፹፬)።

ፍቅሬ ዮሴፍ። (፳፻፩)። *አፍሪካዊ ፊደል።* ዜድ ማተሚያ ቤት።.

Anchinbe. E.A. (2013). Language policy and identity construction: The dynamics of Cameroon’s multilingualisim. John Benjamins Publishing Company.

Anderson, Paul. (2010). Evolution of the Tifanagh scripts in unicode. Individual contribution. For consideration by UTC. https://www.unicode.org/L2/L2010/10278-tifinagh-evolution.pdf.

Ayele B. (1997). Ethiopic, an African writing system: Its history and principles. The Red Sea Press.

Bagley, R. W. (2004). Anyang writing and the Origin of the Chinese writing system. In S.D. Houston (Ed.), The first writing: Script invention as history and process, (pp. 190-249). Cambridge University Press.

Dalby, D. (1967). A survey of the indigenous scripts of Liberia and SierraLeone: Vai, Mende, Loma, Kpelle and Bassa. In M. Guthrie (Ed.), African Language Studies (pp. 1-51). School of Oriental and African Studies.

Desalegn L. (2021). Standardization of Oromo: Orthographic and lexical perspectives. [Unpublished doctoral dissertation]. Addis Ababa University.

Elgahmis, R. (2010). The Ancient African scripts in south Algeria, Niger, Mali and Burkinifaso [PhD Dissertation]. Leiden University.

Errington, J. (2008). Linguistics in a colonial world: A story of language, meaning, and power. Blackwell.

Fishman, J. A. (1988). The development and reform of writing systems. In Ulrich Ammon, Norbert Dittmar, and Klaus J.Mattheier (Eds.), Sociolinguistics: An international handbook of the science of language and society (pp. 1643-1650). Walter de Gruyter.

Gabriela, F. S. (2001). The comparative origin and usage of the Geez writing system of Ethiopia. https://zethio.files.wordpress.com/2014/04/the-comparative-origin-and-usage-of-the-geez-writing-system-of-ethiopia.pdf.

Gebremeskel H. and Abera A. (2020). Linguistic evolution of Ethiopic language: A comparative discussion. International Journal of Interdisciplinary Research and Innovations. 8(1), 1-9.

Ghelawdewos A. (2004b) The magnificence of African written culture and why we must adopt Geez fidel for Ethiopian languages. http://www.africanidea.org)/the_magnificence.html.

Gordon, A. E. (1996). On the origins of the Latin alphabet: Modern views. California Studies in Classical Antiquity, 2,157-170.

Mafundikwa, S. (2000). Afrikan alphabets: The story of writing in Afrika. Mark Batty Publisher

Million M. (2008). Indigenous scripts of African languages. African Journal of Indigenous Knowledge Systems. 6(2). DOI: 10.4314/indilinga.v6i2.26422.

Morawiecki L. (2002). Homo scribens, Res Historica,13, 15-38.

Mulugeta S. (2020). Ethiopic script based Dime orthography. Journal of Studies in Ethiopian Languages, 9, 1-27. ds22n.cc.yamaguchi-u.ac.jp/~abesha/SEL/pub/2020/Mulugeta-2020.pdf.

Mulugeta S. (2016). The Maale orthography in Ethiopic script. Zena Lissan, Journal of Academy of Ethiopian Languages and Cultures, 25(1), 74-99. Addis Ababa.

Roy-Campbell, Z. M. (2006). The State of African Languages and the Global Language Politics: Empowering African Languages in the Era of Globalization. In Olaoba F. A and Michael A. P. (Eds.). Selected Proceedings of the 36th Annual Conference on African Linguistics. Cascadilla Proceedings Project.

Schmandt-Besserat, D. (1996). How writing came about. University of Texas Press.

Sergew H. S. (1972). Ancient and medieval Ethiopian history to 1270. United Printers.